# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

81ኛ ዓመት ቁጥር 270 ግንቦት 30 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ስኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ሚኒስቴሩ ባለፈው የመኸር ወቅት 336 ሚሊዮን በላይ ኩንታል ምርት መሰብሰቡን አስታወቀ

- በመስኖ ከ14 ሚሊዮን በላይ ኩንታል ስንዴ ተሰብስቧል
- 900 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ መሬት በባለሃብት እንዲለማ ሆኗል
- አምስት የርጭት አውሮፕላኖችና 23 ድሮኖች ግዢ ተፈጽሟል

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- በ2014 ባለፉት ዘጠኝ ወራት የመኸር ወቅት 336 ነጥብ 6 ሚሊዮን ኩንታል ምርት መመረቱንና ለመጪው የመኸር ወቅት ዝግጅቶችን እያደረገ እንደሚገኝ የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

በተመሳሳይ ከመስኖ ምርት 14 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ መሰብሰቡን እና 889 ሺህ ሄክታር መሬት በባለሃብት እንዲለማ ማስቻሉን እንዲሁም ለኬሚካል ርጭትና ሌሎች የግብርና አገልግሎቶች የሚውሉ አምስት የርጭት አውሮፕላኖችና 23 ድሮኖችን መግዛቱንም ሚኒስቴሩ አስታውቋል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ ኡመር ሁሴን፤ በትናንትናው ዕለት የተቋሙን የ2014 በጀት ዓመት የዘጠኝ ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ለኢፌዴሪ 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 1ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 5ኛ ልዩ ስብሰባ አቅርበዋል፡፡

ሚኒስትሩ ዕቅዱን ሲያቀርቡ እንደገለፁት፤ ባለፈው የመኸር ወቅት 13 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር በዘር ለመሸፈንና 374 ሚሊዮን ኩንታል ለማግኘት ሲሠራ መቆየቱን አስታውሰው፤ 12 ነጥብ 8 ሄክታር በዘር ተሸፍኖ 336 ነጥብ 6 ሚሊዮን ኩንታል ምርት መሰብሰብ መቻሉን አብራርተዋል፡፡

የተሰበሰበው ምርት ከአምናው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር በአምስት ሚሊዮን ኩንታል ማነስ ያሳያል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ይህ ሊሆን የቻለው በግጭት ምክንያት ያላመረቱ ዞኖች መኖራቸው እና የትግራይ ክልል ሪፖርት

ሚኒስቴሩ ባለፈው የመኸር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

አቶ ኡመር ሁሴን፤










ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

ቢልለኔ ስዩም

# ለሰብዓዊ ድጋፍ ሥራዎች ወደትግራይ

- ሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በጥሬው ተልኳል
- 87 ሺህ ሜትሪክ ቶን ምግብና ከ783 ሺህ ሊትር በላይ ነዳጅ ደርሷል

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ለሰብዓዊ ድጋፍ ሥራዎች ወደትግራይ ሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በጥሬው መላኩንና 87 ሺህ ሜትሪክ ቶን ምግብ እንዲሁም ከ783 ሺህ ሊትር በላይ ነዳጅ መድረሱን የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ቢልለኔ ስዩም ትናንትና ለጋዜጠኞች በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ለሰብዓዊ ድጋፍ ሥራዎች... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “ባለፉት ሦስት ወራት መዳረሻቸውን በፓርኮች ያደረጉ ከ12 በላይ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች

- አቶ ሳንዱካን ደበበ
የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ


ፎቶ፡ አዩብ ተፈሪ

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ መዳረሻቸውን ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ያደረጉ ከ12 በላይ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶች መገኘታቸውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሳንዱካን ደበበ አስታውቁ።

አቶ ሳንዱካን ደበበ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት በዓለም አቀፍና የኮቪድ ወረርሽኝና በሀገራዊ ወቅታዊ ሁኔታው የተነሳ የኢንቨስትመንት መሳብ ሥራው ፈታኝ ሆኖ ቆይቷል።

ከዚያ በኋላ ግን የኮቪድ ወረርሽኝም ሆነ ሀገራዊ ወቅታዊ ሁኔታው በአንጻራዊነት መሻሻል በማሳየታቸው

“ባለፉት ሦስት ወራት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# ኅብረተሰቡ በምናባዊ ግብይቶች ላይ ከመሳተፍ እንዲቆጠብ ብሔራዊ ባንክ አስጠነቀቀ

**በጋዜጣው ሪፖሪተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ኅብረተሰቡ ክሪፕቶ ከረንሲ፣ ቢትኮይንና መሰል ምናባዊ ግብይቶች ላይ ከመሳተፍ እንዲቆጠብ አስጠንቅቋል ።

ባንኩ ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳለው፤ የኢትዮጵያ የገንዘብ መደብ ብር እንደሆነና በብሔራዊ ባንክ በሌላ አኳኋን ካልተፈቀደ በስተቀር በሀገሪቱ የሚከናወኑ ማናቸውም የገንዘብ ግንኙነቶች ሁሉ የሚከፈሉት በብር እንደሚሆን የብሔራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2000 በግልጽ ይደነግጋል።

በመሆኑም በኢትዮጵያ እንደ ክሪፕቶ ከረንሲ፣ ቢትኮይን እና የመሳሰለው ምናባዊ ንብረትን (ዲጂታል መገበያያ ገንዘብ) ለግብይት ወይም ለክፍያ መጠቀም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ያልተሰጠው ድርጊት በመሆኑ ኅብረተሰቡ ከእንደዚህ አይነት ሕገ-ወጥ ተግባር ራሱን እንዲጠብቅ ባንኩ አሳስቧል።

በክፍያ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 718/2003 መሠረት በየትኛውም የክፍያ መፈጸሚያ ሰነድም ሆነ ሥርዓት ያለ ብሔራዊ ባንክ ፍቃድ የገንዘብ ዝውውርም ሆነ ገንዘብ ነክ አገልግሎት መስጠት አይቻልም ያለው ባንኩ በመግለጫው፤ በጥናት ለመረዳት እንደተቻለው በአሁኑ ወቅት ከሕግ እውቅና ውጪ ክሪፕቶ ከረንሲ፣ እንደ ቢትኮይን እና የመሳሰሉት የምናባዊ ንብረት (ዲጂታል መገበያያ ገንዘብ) አገልግሎት በኢትዮጵያ እየተስፋፋ መጥቷል ብሏል ።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
ADDIS ABABA

ይህ ተግባር ከብሔራዊ ባንክ እውቅና ውጪ ከፍተኛ የገንዘብ ዝውውር የሚደረግበት መሆኑን የጠቆመው ብሔራዊ ባንክ በመግለጫው፤ ይህም በወንጀል የተገኘን ገንዘብ ለማሸሽ ምቹ ሁኔታን እየፈጠረ እንደሆነ ለመረዳት መቻሉን ጨምሮ ገልጿል።

እየተስተዋለ ያለው ምናባዊ ንብረትን (ዲጂታል መገበያያ ገንዘብን) ለግብይት ወይም ለክፍያ መጠቀም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ዕውቅና ያልተሰጠው ድርጊት በመሆኑ ኅብረተሰቡ ከእንደዚህ አይነት ሕገ-ወጥ ተግባር ራሱን መጠበቅ ይኖርበታል ብሏል ባንኩ።

ይህን ድርጊት ፈጽመው በሚገኙ አካላት ላይ ብሔራዊ ባንክ ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወስድ አመልክቶ፤ ኅብረተሰቡም ይህንን ሕገወጥ ተግባር የሚሠሩ አካላትን ሲመለከት ለብሔራዊ ባንክ እና ለሚመለከታቸው ሕግ አስከባሪ አካላት ጥቆማ እንዲሰጥ ጥሪውን አቅርቧል።

# አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስም ለአብርኖት ቤተ መጽሐፍት ከ800 በላይ መጽሐፍትን አበረከተ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስም ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት የተለያዩ ይዘት ያላቸው ከ800 በላይ መጽሐፍትን አበረከተ ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት « በዕድሜ ልክ» በሚል ለአብርኆት ቤተመጽሐፍት በ81 አመት ምርጥ መቶ መጽሐፍትን የማሰባሰብ መርሐ ግብር እያከናወነ ይገኛል። ይህን መሠረት በማድረግ አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅም በኢፕድ ስም ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት ከ800 በላይ መጽሐፍትን አበርክቷል ።

በግሉ የትምህርት ዘርፍ አንጋፋ ልምድ ያለው አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የተለያዩ ይዘት ያላቸውና ከ300 ሺ ብር በላይ ግምታዊ ዋጋ ያላቸውን 815 መጽሐፍትን ለአብርሆት ቤተ መጽሐፍት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስረክቧል ።



አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ግምታቸው 300ሺህ ብር በላይ የሆኑ መጽሐፍትን አበርክቷል፤

የአልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ፕሬዚዳንት አቶ ስማቸው አለምነህ መጽሐፍቱን ባስረከቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ ላለፉት 40 ዓመታት ያህል የተማረ የሰው ኃይል በማፍራት ረገድ በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተደራሽ ያደረገ አንጋፋ ተቋም ነው ። ተቋሙ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አጋዥ ከሆኑ አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ካሉት እንቁ የሆኑ መጽሐፍቱ መካከል የቢዝነስ፣ ኢኮኖሚክስ፣ የአካውንቲንግ፣ የፋይናንስና ሌሎች ይዘት ያካተቱ መጽሐፍትን በኢፕድ ስም ለአብርኆት ቤተመጽሐፍት ማስረከባቸውን ገልጸዋል ።

መጽሐፍት ከስጦታዎች ሁሉ ትልቁ ስጦታ በመሆኑ ሌሎች መሰል የግል የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ድጋፍ ሊያደርጉ ይገባልም ብለዋል ።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ ጌትነት ታደሰ መጽሐፍቱን በተረከቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ አልፋ ዩኒቨርሲቲ ያደረገው የመጽሐፍት ስጦታ ትክክለኛውን ነገር በትክክለኛው ቦታ ለማስቀመጥና ጥቅም ላይ እንዲውል ለማድረግ መወሰን ስለሆነ የትኛውም አመራር ሲተገብረው የሚያስደስት ጉዳይ ነው ።

አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ካሉት አስፈላጊ የሚባሉ መጽሐፍት በአብርኆት ቤተመጽሐፍት ተቀምጠው ትውልድ እንዲገለገልባቸው አቅዶና አስቦ ይህን ተግባር በመፈጸሙ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ስም አመስግነዋል።

የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ አበረ አዳሙ በበኩላቸው መጽሐፍት የእውቀት ምንጭ ናቸው። እውቀት የሚገኘው ከመጽሐፍት ነው ።እውቀት ደግሞ ሌባ አይሰርቀውም፣ እሳትም አያቃጥለውም ። አልፋ ያበረከታቸው መጽሐፍትም የእውቀት ምንጭ በመሆናቸው ሊመሰገኑ ይገባል ብሏል ።

የተለያዩ ይዘት ያላቸው ስምንት መቶ 15 መጽሐፍት በኢፕድ በኩል ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት እንዲሰጥላቸው የዩኒቨርሲቲ ኮሌጁ አመራሮችና የቦርድ አባላት በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በመገኘት አበርክተዋል።

አልፋ ዩኒቨርሲቲ ባለፉት 40 ዓመታት የመማር ማስተማር ጉዞው በሂደት የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት ከመቶ ሺ በላይ ማኅበራዊ ኃላፊነቱን እየተወጣ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው ።

# የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ሁለት ሺህ መጽሐፍትን ለአብርኖት ቤተ መጽሐፍት አስረከበ

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት በሁለተኛ ዙር ያሰባሰበውን ሁለት ሺህ መጽሐፍት ትናንት አስረከበ።

ከ38 ቅርንጫፎቹና ከዋናው ማዕከል ሠራተኞች ያሰባሰባቸውን ሁለት ሺህ መጽሐፍት ነው ያስረከበው።

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ሰይፈ ደርቤ መጽሐፍቱን ባስረከቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ ከ38 ቅርንጫፎቹና ከዋና ማዕከል ሠራተኞች የተሰበሰቡት መጽሐፍት ማኅበራዊ ሳይንስ፣ ኪነጥበባዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ትምህርታዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ እጅግ ጠቃሚ ናቸው።

መጽሐፍ የማሰባሰቡ ተግባርም ለሦስተኛ ዙር እንደሚቀጥል ገልጸው፤ መጽሐፍቱን ለአብርኆት ቤተ መጽሐፍት በመስጠታችን ትልቅ ኩራት ይሰማናል ብለዋል ።የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት በመጀመሪያው ዙር አምስት ሺህ 500 መጽሐፍትን ማስረከቡንም አስታውሰዋል፡፡

በርክክቡ ላይ የተገኙት የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማኅበራዊ ዘርፍ አማካሪ ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት መጽሐፍቱ ወደ ትክክለኛ ቤታቸው እንደመጡ ገልጸው፤ የማሰባሰቡ ተግባር እስከሚቀጥለው እሁድ ይከናወናል ብለዋል። ወጣቶች እና ልጆች የወላጆቻቸውን ታሪክ በሚገባ መጠበቅ ከፈለጉ መጽሐፍት ወደ ቤተ መጽሐፍት ሰነዶቻቸውን ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመጽሐፍት እና ቤተ መዛግብት በመውሰድ ለታሪክ እንዲተላለፉ ማድረግ መቻል እንዳለባቸው ተናግረዋል ።የመጽሐፍት ማሰባሰቡ ተግባር ሲጀመር የማሰባሰቡ አካል የሆነውን የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅትን አመስግነዋል፡፡

ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት እንደተናገሩት መጽሐፍት የሰው ልጅ አዕምሮ የሚገነባባቸው ናቸው።የቤተመጽሐፍት ዓላማ ሰዎች በአዕምሮ ዕውቀት ራሳቸውን እንዲችሉ ማድረግ ነው ያሉት ሙዓዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል፤ ሰው ሙሉ ሰው መሆን የሚችለው ዕውቀትም ምግብም ማግኘት ሲቻል ነው ብለዋል፡፡

አብርኆት ቤተ መጽሐፍት አካል ጉዳተኞችን ያማከለና ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል አገልግሎት እንደሚሰጥ ጠቁመው፤ ሁሉም ኅብረተሰብ ከአንድ መጽሐፍ ጀምሮ ማበርከት እንደሚችልም ገልጸዋል ።

በትናንትናው ዕለት ከኢዜአ በተጨማሪ አቶ አንሙት ክንዴ የተባሉ አሁን በሕይወት የሌሉ ግለሰብ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ባደረጉት ኑዛዜ ከ200 በላይ መጽሐፍትን ለአንባቢያን አድርሱልኝ ባሉት መሠረት ሶስት ወዳጆቻቸው ተገኝተው መጽሐፍቶቹን አስረክበዋል ።




ፎቶ፡-እዮብ ተፈሪ

ኢዜአ ከ38 ቅርንጫፎቹና ከዋና ማዕከሉ ያሰባሰባቸውን መጽሐፍት ለግሷል፤

ዜና

# በትግራይ ከተሞች ነዋሪዎች በየደጃፋቸው ሳይቀር እየተገደሉ መሆኑን ቢቢሲ ዘገበ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡-በተለያዩ የትግራይ አካባቢዎች በተለይ ትላልቅ በሚባሉት ከተሞች ሰላማዊ ሰዎች ደጃፋቸው ላይ ጭምር በሌቦችና በዘራፊዎች የሚገደሉበት አሳዛኝ ሁኔታ እየተስፋፋ መሆኑን ቢቢሲ ዘገበ።

በሕግ ማስከበር ዘመቻው ወቅት በሕወሓት ጉዳይ ደጋፊ አቋም በመያዝ ይዘግባል በሚል የሚወቀሰው ቢቢሲ አማርኛ የየከተሞችን ነዋሪዎች አነጋግሮ ባወጣው ዘገባ፤ በአሳሳቢ ሁኔታ እየተፈጸመ ባለው የወንጀል ድርጊት ምክንያት በከተሞች ከባድ የጸጥታ ስጋት አንዣቦ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት ሰላማዊ ሰዎች ከደጃፋቸው ላይ ጭምር በሌቦችና በዘራፊዎች የሚገደሉበት አሳዛኝ ሁኔታ እንዳለ ነዋሪዎች ጠቅሰው፤ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የትግራይ አካባቢዎች በተለይ ትላልቅ በሚባሉት ከተሞች ውስጥ በርካታ ወጣቶች መሳሪያ በመታጠቃቸው ነዋሪዎች ስጋት ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት በበርካታ የትግራይ ከተሞች በተለይ ደግሞ በመቀሌ የሚታዩ የሌብነትና የዘረፋ ወንጀሎች በርካታዎችን ያስጨነቀ ጉዳይ ሆኗል። በከተማዋ ውስጥ ዘረፋና ለዘረፋ ሲባል እስከ ግድያ የሚደርሱ ወንጀሎች እየተፈፀሙ እንደሆነ ይሰማል።

መቀሌ ከተማ ውስጥ በንግድ ሥራ የምትተዳደረውና ስሟ እንዲገለፅ ያልፈለገች ነዋሪ፣ “ሁኔታዎች በጣም ከባድ ሆነዋል። ወጥቶ መግባት አስፈሪ ሆኗል። የመንገድ ላይ ንጥቂያ፣ በሥራ ቦታ ስርቆት እንዲሁም ዘረፋ ያጋጥማል።



እኔ ባለሁበት ቦታ ብዙ ሱቆች ይሰረቃሉ። ይህንን በመስጋት እኔም ጥበቃዎች ሱቄን እንዲጠብቁ እያደረግሁ ነው” ትላለች።

የከተማዋ ነዋሪ እንደምትለው በድፍረት የሚመጡ ዘራፊዎችና ሌቦች የሚፈልጉትን ነገር ያለምንም ፍርሃት ፈጽመው ነው የሚሄዱት።

“ሱቅ ውስጥ ገብተው የሚፈልጉትን ነገር አንስተው ይሄዳሉ፤ አንዳንድ ጊዜም ሙሉ ሸቀጦችን አንስተው የሚሄዱበት አጋጣሚዎችም አሉ። ብዙ የሚያሳዝን ነገር ነው የሚሰማው።”

ዳንኤል የሚባል የከተማዋ ነዋሪ በበኩሉ የደኅንነትና የፀጥታ ስጋቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደሆነ ይናገራል።

ሰዎች በስጋትና በፍርሃት የተወጠሩበት ሁኔታ እንደተፈጠረ በመጠቆም “ብዙ ሰቀቀን ተከስቷል፤ ሰዎች ማምሸት አይችሉም። የሚያመሽ ሰው ሌቦች ሊያገኙት እንደሚችሉ ስለሚያስብ እንቅስቃሴ ተገድቧል” ሲል ያለውን ሁኔታ ይገልጻል።

ይህንንም በመፍራት ዳንኤልም ሆነ በቅርብ የሚያውቃቸው ጓደኞቹና የሥራ ባልደረቦቹ ዘወትር በጊዜ ወደ የቤታቸው ከመግባት በስተቀር ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው ይናገራል።

“ብዙ ነገር ይሰማል። ከሁሉ የከፋው ግን በየሰፈሩ የተቧደኑ ወጣቶች ‘አለው’ ብለው የጠረጠሩት ግን ምንም የሌለውን ሰው ሳይቀር አደጋ እያደረሱበት ነው” ይላል ዳንኤል።

በአሁኑ ወቅት የተለያዩ ነገሮችን ከሰዎች እጅ ላይ ለመዝረፍ ሲባል ሕይወት የሚጠፋበት ሁኔታ በከተማዋ ውስጥ እየታየ፣ እየተሰማ ነው።

ሻይና ቡና በመሸጥ የምትተዳደረው ሰምሃል (ለደኅንነቷ ሲባል ስሟ የተቀየረ) በበኩሏ “ደብረዳሞ” በመባል በሚታወቀው አካባቢ በተደጋጋሚ ሰዎች ተገድለዋል የሚል ወሬ እንደምትሰማ ተናግራለች።

“ሁኔታው በጣም ከፍቷል። የማትገምታቸው ሰዎች ሳይቀር ሌብነትና ዘረፋ ላይ ተሰማርተው ታያለህ። ለዚህ ድርጊትም ሁኔታዎችን አጥንተው የሚመጡ ይመስለኛል” በማለት እሷም የዘረፋ ሰለባ የሆነችበት አጋጣሚ እንዳለ ትገልፃለች።

ስርቆትና ዘረፋው ቀንም ሆነ ማታ ሰው እያየ እንደሚፈጸም ጠቁማ “በእጅ ላይ ያለን ነገር መስጠት ያልፈቀደ ሰውን በስለት ይወጋሉ። ቢኖርህም ባይኖርህም ሕይወትህን እስከማጥፋት ይደርሳሉ። እኛ አካባቢ የሞቱና የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ብዙ ሰዎች አሉ” ትላለች።

ቢቢሲ አማርኛ በቅርቡም የሕወሓትን ገመና ያጋለጠበትን ዘገባ መስራቱ ይታወሳል።

# ትምህርት እንዲቀጥሉ እየሠራ እንደሚገኝ ክልሉ ገለጸ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

አዲስ አበባ፡- በግጭት አካባቢዎች ለ12ኛ ክፍል ተፈታኞች በተሰጠው የዳግም መፈተን ዕድል መሠረት ተማሪዎች ውጤት እንዲያስመዘግቡ የመማር ማስተማር ሂደቱ ክረምቱንም እንዲቀጥል እየሠራ እንደሚገኝ የአማራ ክልል ትምህርት ቢሮ ገለጸ፡፡

የክልሉ ትምህርት ቢሮ ሕዝብ ግንኙነትና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ጌታቸው ቢያዝን በተለይም ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ ዳግም በተሰጠው የመፈተን እድል ተማሪዎቹ ክረምቱን እንዲጠቀሙበት ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ ይገኛል፡፡

ክልሉ ረጅም ጊዜን በጦርነት ውስጥ በማሳለፉ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ዙሪያ የሚጠበቀውን ትምህርት አለማግኘታቸውንና ተረጋግተውም መፈተን አለመቻላቸውንም አስታውሰዋል፡፡

አካባቢው በወረራና በጦርነት ውስጥ በመቆየቱ የክልሉ ሕዝብ ዋና ትኩረቱን ራስን ማዳን ላይ አድርጓል፡፡ ተማሪዎችም የዚሁ አካል ነበሩ፡፡ ስለሆነም ከዚያ ትኩረት እንዲወጡ ከስነልቦና ሕክምና ባሻገር ትምህርቱን የሚሸፍኑበትና ተረጋግተው የሚያጠኑበትን እድል ማመቻቸት ግዴታ እንደሆነም ነው አቶ ጌታቸው የተናገሩት፡፡

ለዳግም ተፈታኞች በመደበኛው የመማር ማስተማር ሥራው ብዙ እድሎች ቢሰጥም፤ በቂ ነው ተብሎ ስለማይታመን የክረምት ትምህርትም እንዲቀጥል መታሰቡን ገልጸዋል፡፡

ትግበራው በጥናት እንዳይዘናጉ በማገዝ የረሷቸውን ነገሮች እንዲያስታውሱ ለማድረግ ያግዛል፣ ያልሸፈኗቸው ቦታዎች ካሉም ለመሸፈንና ለፈተና ዝግጁ እንዲሆኑ ያስችላቸዋልም ብለዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ መደበኛ የትምህርት ሥርዓቱ ከሰኔ 30 በኋላ ትምህርት የሚያበቃ ቢሆንም ትምህርት እንዳይቋረጥ ይደረጋል፣ ሐምሌና ነሐሴን ተፈታኞቹ ሳይዘናጉ ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ዳግም ተፈታኞችም ሆኑ መደበኛ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ልዩ ትኩረት ይፈልጋሉ ያሉት አቶ ጌታቸው፤ እንደ ትምህርት ቢሮ ልዩ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ከማኅበረሰብ ጋር ውይይት መደረጉን፣ ጥሩ ምላሽም በመገኘቱም የክረምት ትምህርቱ እንደሚቀጥልም ነው የጠቆሙት፡፡

ይህንን የፈተና ጊዜ ለማለፍ መምህራን ከምንም በላይ እየተጉ መሆናቸውን የተናገሩት አቶ ጌታቸው፤ የዘንድሮ ውጤት ተማሪውን ብቻ ሳይሆን የክልሉን ነዋሪ ጭምር ልብ የሰበረ እንደነበርም አስታውሰዋል፡፡

በተለይ መምህራንን በእጅጉ አዝነው ነበር ያሉት ኃላፊው፤ ቁጭታቸውን ለመወጣት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በማስተማር ላይ እየተጉ እንደሚገኙም ተናግረዋል፡፡ በተመሳሳይ ተማሪዎቹም በክረምት መርሐ ግብሩ እንደሚደሰቱ አመልክተዋል፡፡

# የትርጉም ጥራትን የሚለካ ተቋም ባለመኖሩ የትርጉም ሥራዎች ጥራት ጉድለት እየታየባቸው መሆኑን ጥናት አመለከተ

**ሶሎሞን በየነ**

አዳማ፡- በኢትዮጵያ የትርጉም ጥራት የሚለካና ዘርፉን የሚቆጣጠር ተቋም ባለመኖሩ አብዛኞቹ የትርጉም ሥራዎች ጥራታቸው የተጓደለ፤ ክፍተትና ስህተት ያለባቸው መሆኑን ጥናት አመለከተ።

ትናንት ሁለተኛው ሀገራዊ የትርጉም ጉባኤ “translation for national consensus (ትርጉም ለሀገራዊ መግባባት) “በሚል መሪ ሃሳብ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ከአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር በአዳማ ከተማ ተካሂዷል።

በጉባኤው “የትርጉም ሙያዊነት በኢትዮጵያ” በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፍ ያቀረቡት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፈረንሳይኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ኃላፊ ረዳት ፕሮፌሰር ዮሐንስ በየነ እንደገለጹት፤ የትርጉም ሥራ በሀገሪቱ ለረጅም ጊዜ ሲሠራበት ቆይቷል። ሆኖም ግን በሀገሪቱ የትርጉም ጥራት የሚለካና ዘርፉን የሚቆጣጠር ተቋም ባለመኖሩ የትርጉም ሥራዎች ጥራታቸው የወረደ መሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል።

እንደእርሳቸው ማብራሪያ፤ በኢትዮጵያ የትርጉም ሥራ ዕልፍ ዘመን ቢያስቆጥርም ሙያው ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾለት በዲግሪ፣ በማስተርስ ወይም በዶክትሬት ዲግሪ እየተሰጠ አይደለም። በዚህም በሀገሪቱ የትርጉም ሥራ በሳይንሳዊ መንገድ ሳይሆን በዘልማድ እየተሠራ ይገኛል።

ስለዚህ የትርጉም ሥራን በበላይነት የሚመራ፣ የሚያስተዳድር እንዲሁም የሚቆጣጠር ተቋም ባለመኖሩ ብዙዎቹ የትርጉም ሥራዎች ክፍተትና ስህተት አለባቸው። ጥራት ባለው ደረጃ አይደለም እየተሠራ ያለው ብለዋል ረዳት ፕሮፌሰር ዮሐንስ።

በተጨማሪም የማስተማሪያ መጽሐፍት ቀጥታ ከእንግሊዘኛ ወይም ከሌሎች ቋንቋዎች ወደ ሀገሪቱ መማሪያ ቋንቋዎች ተተርጉመው ነው ለተማሪዎች የሚቀርቡት። ስለዚህ የትርጉም ሥራ ጥራት መጓደሉ በትውልድ ላይ ለመግባባት እንከን ሲፈጥር ይስተዋላል።

የፖለቲካ ወይም የፖሊሲ ሰነዶች ጥራት ባለው ደረጃ ካልተተረጎሙ በሀገር ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተጽዕኖ ከባድ ነው። ይህ ክፍተት ደግሞ አለመረዳዳትን ይፈጥራል። አለመረዳዳት ደግሞ እንደሀገር አለመግባባትን ይፈጥራል ብለዋል።

በገጽ፣ በቃላት፣ በጥራዝና በመሳሰሉት የትርጉም



ረዳት ፕሮፌሰር ዮሐንስ በየነ

ሥራዎችን የሚያስከፍሉ የትርጉም ድርጅቶች መኖራቸውን ጠቁመው፤ መስፈርት ስለሌለ የማስተርጎሚያ ዋጋ የዋዠቀና የተለያየ ነው። ወጥነትም የለውም ብለዋል።

ስለዚህ የትርጉም ሥራን በበላይነት የሚመራ ተቋም ቢኖር ባለሙያው ትክክለኛ የሥራውን ዋጋ እንዲያገኝ በአንጻሩ ደግሞ ተገልጋዩ ማኅበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ አገልግሎቱን እንዲያገኝ ያስችላል። በጥቅሉ የትርጉም ሥራን በበላይነት የሚያስተዳድር ተቋም ቢቋቋም የባለሙያውን የብቃት ደረጃ ያረጋግጣል የሚሠሩ የትርጉም ሥራዎች ጥራት ይከታተላል ነው ያሉት፡፡

በየትኛውም ቦታ ለሚሠሩ የትርጉም ሥራዎች መመዘኛ መስፈርት በማውጣት ወጥነትና ጥራት ያለው ሥራ እንዲሠራ፣ የአስተርጓሚዎች ማኅበራት ለማቋቋም ይረዳል እንዲሁም በቀጣይነት እና በዘላቂነት ለባለሙያዎች ስልጠና ለመስጠትና ዘርፉን ለማልማት ያስችላል። ስለዚህ መንግሥት የተቋሙ መቋቋም ያለውን ፋይዳ ከግምት በማስገባት ተቋሙን በማቋቋም ድርሻውን ሊወጣ እንደሚገባ ረዳት ፕሮፌሰሩ አሳስበዋል።

# በኮንስትራክሽን ዘርፎች ሴቶችን ተጠቃሚ እያደረገ መሆኑን መምሪያው አስታወቀ

አስናቀ ፀጋዬ

ሃዋሳ፡- በከተማ በሚከናወኑ ፕሮጀክቶች ውስጥ ሴቶችን በማሳተፍ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ እየሠራ እንደሚገኝ የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ አስታወቀ ።

የሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ልማትና ኮንስትራክሽን መምሪያ ምክትል ኃላፊ አቶ ታሪኩ ታመነ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤በኮንስትራክሽን ዘርፎች ሴቶችን በማሳተፍ ተጠቃሚነታቸውን ለማሳደግ እየተሠራ ይገኛል ።

በዩ አይ ዲ ፒ በሚደገፈው የኮብል ስቶን መንገድ ሥራ ፕሮጀክት ሰፊ ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ይሳተፋሉ ።በሥራው ሴቶች ሃምሳ ከመቶ ከወንዶች እኩል እንዲወዳደሩ በማድረግ ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚገኙ አቶ ታሪኩ ገልፀዋል ።

ተወዳድረው ከሚያሸንፉ ማኅበራት በርካታ ሴት ወጣቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንደተቻለም ኃላፊው አስታውቀዋል ።በሌሎች ፕሮጀክቶችም ድጋፍ በማድረግ የተለያዩ ጨረታዎች ሲወጡ ቅድሚያ ለሴቶች በመስጠት ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ እንዳሉም ጠቁመዋል፡፡

በርካታ ሞዴል የሆኑ ማኅበራት እንዳሉና በተለይ በኮብል ስቶን መንገድ ሥራና በሼዶች ውስጥ ገብተው በአገልግሎትና በንግድ ዘርፎች ውስጥ የተሰማሩ ማኅበራት ራሳቸውን በማብቃት ረገድ ትልቅ ደረጃ መድረሳቸውንም ኃላፊው አመልክተዋል ።

በተያዘው በጀት ዓመት በኮብል ስቶን መንገድ ሥራ ከ200 ሺ በላይ ወጣቶች የዕድሉ ተጠቃሚ መሆናቸውንም ገልጸዋል ።ከዚህ ውስጥ ከሀምሳ ከመቶ በላይ የሚሆኑት ሴት ወጣቶች መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

ሴቶቹ ተሳታፊ ከመሆን በዘለለ ሴት ፎርማንና ሴት ኢንጂነሮች ላሉባቸው ማኅበራት ቅድሚያ እንደሚሰጥና የመሪነት ሚናቸውንም በዚህ ፕሮጀክት እየተወጡ እንደሚገኙም ጠቁመዋል ።

ሴቶች በኮንስትራክሽን ዘርፍ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከማድረግ በዘለለ መብታቸውን እንዲጠቀሙ በማድረግና በማብቃት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑንም ኃላፊው ጠቅሰዋል ።ከዩ አይ ዲ ፒ በሚመደብላቸው በጀት የተለያዩ ስልጠናዎችን ራሳቸው አዘጋጅተው ራሳቸው እንዲሰጡ እየተደረገ እንዳለም አስታውቀዋል።

የሲ አይ ፒ እቅድ ዝግጅት ላይ ሴቶች ለብቻቸው እንዲወያዩ፣ እንዲወስኑ፣ ለየትኛው ፕሮጀክት ቅድሚያ መስጠት እንዳለበትና ፕሮጀክቱ ሲያልቅ ምን ያህል ሴቶች ተጠቃሚ እንደሚሆኑና መሳተፍ እንዳለባቸው በመምሪያው በኩል ሰፊ ሥራ እየተሠራ እንዳለም ኃላፊው ገልፀዋል ።

በቀጣይነትም ሴቶች መብታቸውን እንዲያውቁና አቅም እንዲያጎለብቱ በተመሳሳይ መልኩ ሥራዎች እንደሚሠሩና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀጥሉ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እየተሠራ እንደሚገኝም አመልክተዋል ።

ፎቶ፡- በሃዲሽ አብርሃ



አቶ ታሪኩ ታመነ፤

# “ባለፉት ሶስት ወራት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባለፉት አራትና ሦስት ወራት ውስጥ የሀገር ውስጥም የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት ፍሰቱም በተለይ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ጨምሯል ብለዋል።

ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ ወደኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ገብተው የሚያለሙ ከ12 በላይ ኢንቨስትመንቶች መገኘታቸውን ጠቁመዋል።

እነዚህ አዲስ ኢንቨስትመንቶች የውጭ ሀገራትንም ሆነ የአገር ውስጡን ያማከሉ ናቸው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ እያንዳንዳቸው በቢሊዮን ብር የሚቆጠር ሃብት ያላቸው ኩባንያዎች ናቸው። ኢንቨስትመንቶቹ በግብርና፣ በሕክምና ዕቃዎች እንዲሁም በተለያዩ የምርትና አገልግሎት ዘርፎች መሰማራታቸውን ገልጸዋል።

ኢንቨስትመንቶቹ በሥራ ዕድልም ሆነ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት ዕድገት ረገድ ለሀገራችን የበኩላቸውን ሚና እንደሚወጡ ይጠበቃል ሲሉም ተናግረዋል።

በአሁኑ ጊዜ በብዙ መንገድ ከበፊቱ የተሻለ ሁኔታ ላይ ነው ያለነው። ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ግንባታ ላይ የነበሩት ኢንዱስትሪ ፓርኮቻችንም ተጠናቀው አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል፤ ኢንዱስትሪ ፓርኮቻችን በመሠረተ ልማትም ሆነ በአሠራር ሥርዓት አኳያ የተሻሉ ናቸው ብለዋል።

በተጨማሪ ሀገራዊ ወቅታዊ ሁኔታውም በተመለከተ አሁን ላይ ኢንቨስትመንት መጋበዝ የሚያስችል አንጻራዊ መረጋጋት አለ። በመሆኑም ከእስካሁኑ በበለጠ ትላልቅ ኢንቨስትመንቶችን የምንጠብቀው በቀጣይ ጊዜያት ነው። የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የሚያመላክተውም ይሄንኑ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ኢንቨስትመንት በብዛት እንዲመጣ ያሉትን አማራጮች ሁሉ በመጠቀም እየተሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ሳንዱካን፤ እኛም ካለው የፖለቲካና ኢኮኖሚክ ትብብር አንጻር ይበልጥ ትኩረት አድርገን የምንሠራባቸው አህጉራት አሉ ብለዋል።

አሁን ላይ በአብዛኛው ኢንቨስትመንቶች እየመጡ ያሉት ከእስያ በተለይም ከቻይና ፣ ሕንድ እንዲሁም ከመካከለኛው ምስራቅ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በሌላ በኩል ከአሜሪካና ከአውሮፓም የሚመጡ ኢንቨስትመንቶች መኖራቸውን ገልጸዋል።

ባለፉት ሁለትና ሶስት ሳምንታት እንኳን የመረቅናቸውና የተቀበልናቸው ኢንቨስትመንቶች አንዳንዶቹ ዋና መቀመጫቸውን አሜሪካ ያደረጉ ሲሆኑ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ አውሮፓ ውስጥ መሠረት ያደረጉና ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ኢንቨስትመንቶች ናቸው ብለዋል።

ለአብነት ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የገባውና ከ50 ሺህ በላይ አርሶ አደሮች ጋር ትስስር የፈጠረው የገብስ ብቅል አምራች ፋብሪካ መሠረቱን ያደረገው በፈረንሳይ አገር ሲሆን፤ ሌላኛው በካይ ያልሆኑ ታዳሽ ኃይሎች ላይ ኢንቨስት የሚያደርገው የአውስትራሊያው ኩባንያ ካየን ኢንቨስትመንቶች ከተለያዩ ሀገራት እየመጡ መሆኑን እንረዳለን ብለዋል።

ይህ ከተለያዩ ሀገራት ወደ ኢትዮጵያ የሚመጣው የተጠናከረ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ በቀጣይ ጊዜያትም እየጎለበተ እንደሚሄድ ተስፋ አለን። ለዚህም ኢንቨስትመንት በመሳብ ረገድ የምናደርገውን ጥረት አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉ ተናግረዋል።

በ2014 በጀት ዓመት ባለፉት ዘጠኝ ወራት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ተመርቶ ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች 152 ሚሊዮን 766 ሺህ 261 የአሜሪካን ዶላር መገኘቱንና፤ ባለፉት ዘጠኝ ወራት ለባለሀብቶች በኪራይ ከተላለፉ 135 ሼዶች ውስጥ 98 የሚሆኑት ማምረት መጀመራቸውም ኮርፖሬሽኑ ማስታወቁ ይታወሳል።

በተጨማሪ በ2014 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ወደ ሥራ ከገቡ ድርጅቶች 44 ሺህ 292 የሥራ ዕድል መፈጠር መቻሉን ኮርፖሬሽኑ ገልጿል።

# ለሰብዓዊ ድጋፍ ሥራዎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሰሜኑ የሀገሪቷ ክፍል ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም አንስቶ እስከ ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም ባለው መረጃ መሠረት ወደትግራይ ለሰብዓዊ ድጋፍ ሥራዎች ሁለት ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በጥሬው መላኩንና በተጨማሪ 87 ሺህ ሜትሪክ ቶን ምግብ ወደትግራይ መግባቱን ቢልለኔ ስዩም አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል ከ217 ሺህ ኪሎግራም በላይ የመድኃኒት አቅርቦት ወደትግራይ እንዲደርስ መደረጉንና፤ ምግብ ነክ ያልሆኑ የሰብዓዊ ድጋፎችን በተለይም የመጠለያ ግብዓቶች በመለከተ 130 ሺህ ኪሎግራም የሚመዝን የሰብዓዊ ድጋፍ ወደትግራይ መላኩን ተናግረዋል።

በሚያዚያና ግንቦት ወራት የሰብዓዊ ድጋፍ ያጓጓዙ 1 ሺህ 306 ተሽከርካሪዎች ወደትግራይ መግባታቸውን ጠቁመው፤ በተጨማሪም የሰብዓዊ ድጋፍ የሚያቀርቡ የአየር በረራዎችም መደረጋቸውን ገልጸዋል።

ነዳጅ በተመለከተ ከ783 ሺህ ሊትር በላይ ነዳጅ ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም አንስቶ እስከ ግንቦት 26 ቀን 2014 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ ወደትግራይ ክልል ተልኳል ብለዋል።

መንግሥት ያልተገደበ የሰብዓዊ ዕርዳታ ድጋፍ እንዲቀርብ ከወሰነ ጊዜ አንስቶ የተለያዩ ድጋፎች እንዲደረጉ አስፈላጊውን ትብብር እያደረገ ይገኛል ያሉት ፕሬስ ሴክሬታሪያት ኃላፊዋ፤ መንግሥት ለሰብዓዊ ዕርዳታ ያለውን ቁርጠኝነት ባሳየበት ወቅት ግን በተለይም ባለፉት አራት ሳምንታት የሕወሓት ቡድን ለተጨማሪ ጥቃትና ወረራ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ጠቁመዋል።

ይህ የወረራ ግፊት በሚያሳዝን ሁኔታ መጪውን የግብርና ወቅት ታኮ የመጣ መሆኑን ጠቁመው፤ አሸባሪው ሕወሓት ባለፉት ሳምንታት እንዳደረገው የጦርነት ጉሰማውን ከቀጠለ የትግራይን ክልል ነዋሪ ለኪሳራ የሚዳርግና በክልሉ ግብርና ሥራ ላይ መጥፎ ተጽዕኖ የሚያሳድር ይሆናል ሲሉ የችግሩን አሳሳቢነት አስረድተዋል።

አሸባሪው ሕወሓት የትግራይ ነዋሪዎችን በኃይል ወደ ቡድኑ ለመቀላቀልና ለጦርነት ለመማገድ ጥረት እያደረገ መሆኑን የተለያዩ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህ ዓይነቱ የጥፋት መንገድ አይጠቅምም ሲሉም ተናግረዋል።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ መንግሥት ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት አሳይቷል። በተጨማሪ በክልሉ የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ ጥረት እያደረገ ነው። ይሁንና ገለልተኛ ወገኖችም ወደትግራይ የሚገባው የሰብዓዊ ድጋፍ ምን ያክል ለታለመላቸው ዜጎች በፍትሐዊነት እየደረሰ ነው የሚለውን ማጣራት አለባቸው ብለዋል።

ከትግራይ ክልል ባለፈ በአፋር ክልል ላይ 19 ሺህ ሜትሪክ ቶን ምግብ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች መቅረቡን የገለጹት ቢልለኔ፤ በአማራ ክልል በተመሳሳይ ከግጭት ጋር ተያይዞ በተከሰተ መፈናቀል ለችግር ለተጋለጡ ዜጎች ከ244 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ ምግብ ለተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች መሰራጨቱን አስታውቀዋል።

በድርቅ ለተጎዱ ዜጎች በተደረገው ድጋፍ መንግሥት አስፈላጊውን የሰብዓዊ ዕርዳታ መቅረቡን ተናግረው፤ ከኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በተገኘው መረጃ መሠረት ከሐምሌ ወር 2013 ዓ.ም አንስቶ እስከ ግንቦት ወር 2014 ዓ.ም ድረስ በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ሶስት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ዜጎች የምግብ ዕርዳታ ማግኘታቸውን ጠቁመዋል።

ድጋፍ ያገኙት ዜጎች በአብዛኛው በኦሮሚያ፣ በሱማሌና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የሚገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በሌላ በኩል መንግሥት በተለያዩ ክልሎች በሚወስዳቸው የሕግ ማስከበር ዕርምጃዎች በንጹሓን ዜጎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የእራሱን ጥንቃቄ ይወስዳል ብለዋል።

በአማራ ክልል ከተከሰተው ጦርነት በኋላ እራሳቸውን እያደራጁ የመጡ ኃይሎች አሉ፤ በክልሉ መንግሥት ዕውቅና የሌላቸውና የታጠቁ ቡድኖች ላይ ዕርምጃ ተወስዷል። ክልሉም በሕገወጥ መንገድ የተያዘ ትጥቅ የማስፈታትና ሰላምና ጸጥታን የማስከበር ውጤታማ ሥራ አከናውኗል ሲሉ ተናግረዋል።

# ሚኒስቴሩ ባለፈው የመኸር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባለመካተቱ መሆኑን አስረድተዋል ።

ለመጪው መኸር ወቅትና ለሌሎች ጊዜያት ምርቶች 12 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል የማዳበሪያ ግዢ መፈፀሙን አስታውቀው፤ ከዚህ ውስጥ 83 በመቶ የሚሆነው ጅቡቲ ወደብ መድረሱንና 7 ነጥብ 7 ሚሊዮን ኩንታል የአፈር ማዳበሪያ ወደ ክልሎች እንደተጓጓዘ አብራርተዋል ። ሦስት ሚሊየን ኩንታል የሚሆነው ለአርሶ አደሩ መሠራጨቱንም ሚኒስትሩ ገልፀዋል ።

በተመሳሳይ የመስኖ ስንዴ ምርትን አስመልክቶ ማብራሪያ የሰጡት አቶ ኡመር፤ በምርት ዘመኑ 400 ሺህ ሄክታር በማልማት 16 ሚሊዮን ኩንታል ለመሰብሰብ መታቀዱን አስታውሰው፤ በመጀመሪያ ዙር ብቻ 405 ሺሕ ሄክታር በማልማት 14 ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ኩንታል መሰብሰብ መቻሉን ተናግረዋል ።

በሁለተኛ ዙር የምርት ዘመን በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች በድምሩ 160 ሺህ ሄክታር በላይ በዘር መሸፈን መቻሉንና ከዚህም ከ20 ሚሊዮን በላይ ኩንታል ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚገመት ሚኒስትሩ አብራርተዋል ።

በግብርና ኢንቨስትመንትም በሰብል ልማትና በእንስሳት ዘርፍ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ጥረት ሲደረግ እንደቆየ የግብርና ሚኒስትሩ አቶ ኡመር ገልፀዋል ።

ከዘርፉ ባለፉት ዘጠኝ ወራት 889 ሺህ ሄክታር በማልማት 19 ነጥብ 4 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተገኝቷል ። በሌላ በኩል በእንስሳት ኢንቨስትመንት የግል ባለሀብቱን ተሳትፎ በማሳደግ ከ26 ሺህ በላይ የእርድ ከብት፣ ከ172 ሺህ በላይ የሥጋ ዶሮ እና ከ9 ሚሊየን በላይ እንቁላል ማቅረብ ተችሏል ብለዋል ።

ዘርፉ ላይ የሚታዩ ውስንነቶች ያሉ መሆኑን የጠቆሙት ሚኒስትሩ፤ ዋና ዋና የሚባሉት ምክንያቶች የፋይናንስ አቅርቦት እና የባለሃብቱ የልማት ተሳትፎ ውስንነት መሆናቸውን አብራርተዋል ።

የሰብል ተባይ በሽታ የመከላከል አቅምን በማሳደግ ረገድ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ እንደሆነም አቶ ኡመር ተናግረዋል ። በበጀት ዓመቱ በሰብል ልማት ላይ የሚደርሰውን የተባይና በሽታ ጉዳት ለመቀነስ አምስት የርጭት አውሮፕላኖች እና 23 ድሮኖች ግዢ መፈፀሙን በመግለፅ ለአውሮፕላን ማረፊያ ሜዳ ጥገና ለክልሎች 5 ነጥብ 3 ሚሊየን ብር ድጋፍ ተደርጓል ብለዋል ። ይህም በየጊዜው እየተፈታተነን ያለውን የድህረ ምርት ብክነት ለመቀነስ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል ሲሉ ገልፀዋል ።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ለፌዴራል ፖሊስ የተሰጠው እውቅና የሚመጥነውና ለቀጣይ ግዳጅ ዝግጁነቱን የሚያጠናክር ነው!

የአንድ ሀገር ሕልውናም ሆነ የሀገረ መንግሥቱ ጥንካሬ ከሚለካባቸው ዋነኛ መመዘኛዎች መካከል አንዱ የተቋማት ግንባታና የግንባታ ስኬት ነው። ይህ አጠቃላይ የሆነውን የሲቪል ሰርቪስ ፣ የጸጥታ ፣የደህንነት እና የመከላከያ ተቋማትን የሚመለከት ነው። ለዚህም ሲባል ሀገራት ለተቋማቱ ግንባታ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ቀን ከሌት ሲተጉ ይስተዋላል ።

እነዚህን ተቋማት በመገንባት ሂደት ውስጥ የተሳካላቸው ሀገራት ጠንካራ ሀገረ መንግሥት በመመሥረት አጠቃላይ የሆነውን ሀገራዊ ፖለቲካዊ ፣ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሕይወት የተሻለ በማድረግ ለሕዝቦቻቸው የተሻሉ ዛሬዎችን መፍጠር ፤ ነገዎቻቸውንም በተሻለ ተስፋ እንዲጠብቁ ማድረግ ችለዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከፍ ያለ የእድገት ደረጃ ላይ የደረሱ ሀገራት ከዕድገታቸው ሚስጥር አንዱም እነዚህ በከፍተኛ ጥንቃቄ ትውልድ ተሻጋሪ ሆነው በጠንካራ መሠረት ላይ ያዋቀሩዋቸው የብሔራዊ ተቋሞቻቸው ጥንካሬ ሲሆን በቀጣይም ለሚያልሟቸው ህልሞች ስኬት መሠረት እንደሆኑም ይታመናል።

በሀገራችን ኢትዮጵያም እንደሀገር ሀገረ መንግሥቱን በዘመናዊ ጠንካራ መሠረት ላይ ለማዋቀር ከ1933 ዎቹ ዓ.ም ጀምሮ ሰፊ እንቅስቃሴዎች ሲደረጉ ቆይተዋል። ሀገረ መንግሥቱን የሚሸከም ዘመናዊ የሲቪል ሰርቪስን ጨምሮ የጸጥታ ፣የደህንነት እና የመከላከያ ተቋማት የመገንባት ጥረቶች ተደርገዋል።

ጥረቶች በየወቅቱ በሀገሪቱ በሚከሰቱ የፖለቲካ አለመረጋጋቶች ምክንያት የታሰበውን ያህል ውጤታማ ባይሆኑም ፤ ሀገርን እንደ ሀገርም ሆነ ሀገረ መንግሥቱን በማስቀጠል ሂደት ውስጥ የነበራቸው አስተዋጽዖ ግን ከፍ ያለ ነበር። በየወቅቱ ለፖለቲካ ሥርዓቱ እንዲመቹ ሆነው እየፈረሱ የመገንባታቸው እውነታም ለተቋማቱ ዕድገትና ጥንካሬ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ሆኖባቸው ቆይቷል ።

ከሁሉም በላይ በየወቅቱ የነበሩ የፖለቲካ ሥርዓቶች ለሕልውናቸው ተቋማቱን የፖለቲካ መሣሪያ በማድረግ የሄዱበት የተዛነፈ መንገድ ተቋማቱ በነጻነት የተጣለባቸውን ሀገራዊና ሕዝባዊ ኃላፊነት እንዳይወጡ ያደረጋቸው ሲሆን ፤በሕዝብ ዘንድ ያላቸውን ተቀባይነት አሳጥቷቸዋል፤ ለተልዕኳቸው ስኬት ዋነኛ ተግዳሮት ሆኖባቸዋል።

ችግሩ አጠቃላይ በሆነው ሀገራዊ ፖለቲካዊ ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገት ላይ የጎላ ተጽዕኖ ሲፈጥር ቆይቷል። ከዚያም አልፎ አሁን በሀገሪቱ ለሚስተዋሉ ችግሮች ተጠቃሽ ምክንያት ሆኖ ይገኛል። ችግሮቹን ለዘለቄታው ለመፍታትም ተቋማቱን በጠንካራ መሠረት ላይ የማዋቀሩ እውነታ ወሳኝ እንደሆነም ይታመናል።

ከዚህ በመነሳትም የለውጥ ኃይሉ ወደ ሥልጣን ከመጣበት ዕለት ጀምሮ ለተቋማት ግንባታ ትኩረት በመስጠት ሰፋፊ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል። በተለይም በጸጥታ ፣ በደኅንነት እና በመከላከያ ተቋማት ላይ እያደረጋቸው ያሉ የሪፎርም ሥራዎች ሀገሪቱንና ሀገረ መንግሥቱን በጠንካራ መሠረት ላይ በማዋቀር የተጀመረው የብልጽግናና የልማት ጉዞ ስኬታማ ለማድረግ የሚያስችል አቅም በመፍጠር ላይ ይገኛል።

የለውጥ ኃይሉ በአንድ በኩል ተቋማቱን ሀገራዊ በሆነ የአስተሳሰብ መሠረት ላይ በማዋቀር፤ በሌላ በኩል ተቋማቱ የተጣለባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት የሚወጡበትን ሁለንተናዊ ቁመና ለመፍጠር እየሄደበት ያለው መንገድ ፤ብዙ ልፋትና ድካምን የሚጠይቅ ቢሆንም ሀገርና ሕዝብን በማሻገር ሂደት ውስጥ የሚኖረው አስተዋፅዖ በታሪክ ውስጥ የጎላ እንደሚሆን ይታመናል።

ከዚህ ተጨባጭ እውነታ በመነሳትም መንግሥት የፌደራል የፖሊስ ኃይሉን በአዲስ ሕዝባዊ አስተሳሰብ መሠረት ላይ በማዋቀር ፤ከዛም አልፎ የተሰጠውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት የሚያስችለውን ቁመና በመፍጠር ላለፉት ሶስት ዓመታት የሄደበት የሪፎርም መንገድ የሚበረታታ እና እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

የፌደራል ፖሊስ ባለፉት ሶስት ዓመታት ከዕለት ተዕለት የፀጥታ ማስከበር ሥራው ባለፈ ሀገርን ከመፍረስ አደጋ ለመታደግ ከመከላከያና ከሌሎች የጸጥታ ኃይሎች ጋር በመሆን ዘምቶ የፈጸመው ተጋድሎና ያስመዘገባቸው ድሎች የቱን ያህል በጠንካራ ሀገራዊና ሕዝባዊ አስተሳሰብ መሠረት ላይ የተዋቀረ እንደሆነ በተጨባጭ ያሳየ ነው። ይህንን እውነታ ከግንዛቤ በማስገባት በአደባባይ የተሰጠውም እውቅና የሚመጥነውና ለቀጣይ ግዳጅ ዝግጁነቱን የሚያሳድግ ነው!

---

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የኅብረት ሥራ ማኅበራት ገበያን የማረጋጋት ተልዕኮና ተግዳሮቶች

**ሰላማዊት ውቤ**

የኑሮ ውድነቱን ለማርገብና የዋጋ ንረቱን ለማረጋጋት አዲስ አበባ ከተማ ላይ የእሁድ ገበያ ሲጀመር እኔን ጨምሮ ብዙዎቻችን የኅብረተሰብ ክፍል በእጅጉ ደስ ብሎን ነበር። በእርግጥም የመጀመሪያዎቹ ሰሞን የእሁድ ገበያ እንደታሰበው ምግብ ነክና ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ በማቅረብ ገበያውን ማረጋጋትና የኑሮ ውድነቱን ጫና በመጠኑም ቢሆን ማቃለል ችሏል። የግብርና ምርቶች በተለይም አትክልት፣ ጥራጥሬ እና የመኸር ሰብል ምርቶች እንዲሁም የፋብሪካ ምርቶች በተሻለ አቅርቦት እና በተመጣጣኝ የገበያ ዋጋ ለሸማቾች ማድረሱ አስደሳችና ተፈላጊ ነው ። በከተማዋ 50 ቦታዎች ገበያዎቹ መስፋፋታቸው ገበያውን ተደራሽ ስለሚያደርገው በእጅጉ ይበረታታል።

እንደልብና በአቅራቢያ መሸመት ያስችልና መጨናነቅን ይቀንሳል። ኅብረተሰቡ ፓስታና ማኮሮኒውን ጨምሮ፣ዘይቱ ፣ሩዙ፣ ጤፉና ሌሎችም የበሰሉ ምግቦች በተመጣጠነ ዋጋ ቀርበውለት ሲሸምት ቆይቷል። ለአብነት ከበሰሉ ምግቦች አንድ ነጭ ጤፍ ደረቅ እንጀራ በስምንት ብር የቀረበበት ሁኔታም ነበር። ይሄ እነዚህ ምርቶች በእሁድ ገበያ የቀረቡበት ዋጋ ኅብረተሰቡ በሰርኩና በመደበኛው ወቅት ከሚሸምትበት በእጅጉ የተሻለ ነበር።

ከሸማች ማኅበራት ከሚገዛበትም እንዲሁ የተሻለ ሆኖ ቆይቷል። በደምሳሳው የእሁድ ገበያ አሁን ያለውን የዋጋ ንረት ለማረጋጋት እና በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች ያለባቸውን የኑሮ ጫና በመቀነስ ረገድ ጉልህ ሚና ሲጫወት ቆይቷል ። አምራቹን እና ሸማቹን በቀጥታ በማገናኘት በከተማዋ የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል እና ጤናማ የግብይት ሥርዓት እንዲፈጠር ማስቻሉ እሰየው ያሰኛል። ሆኖም አሁን ላይ በከተማችን የእሁድ ገበያ ቀድሞ በነበረበት በዚህ ውጤታማነት ቀጥሏል ለማለት የማያስደፍሩ ብዙ ሕጸጾች ይስተዋላሉ።

በሰርክ ቀናት በሸቀጦችና በምርቶች ላይ የሚታየው የዋጋ ንረት በእሁድ ገበያ ምርቶች ላይም ጎልቶ እየተንፀባረቀ የመጣበት ሁኔታ ተከስቷል። በሸማቾች ማኅበራት ቀደም ሲል ከ30 ብር እስከ አርባ ብር የነበረው አንድ ኪሎ ሩዝ በአብዛኞቹ የእሁድ ገበያዎች በአንድ ጊዜ ከ48 እስከ 50 ብር ማሻቀብ ችሏል። ማኮሮኒም በኪሎ 51 ብር እየተሸጠ እንዲሁ ቀይ የፈረንጅ ሽንኩርት በአንድ ጊዜ ከ40 እስከ 48 ብር የገባበት ሁኔታ መኖሩንም ታዝቤያለሁ። እንዲህም ሆኖ ሽንኩርት አንድ ኪሎ ብቻ አለመሸጡ ብዙዎቹን አቅመ ደካማ ሸማቾች ማሳዘኑንም ሳልታዘብ አላለፍኩም።

አምስት አንዳንዴም ሦስት ኪሎ እንዲገዙ መገደዱ ከዋጋው ንረት በላይ ሲያስቸግራቸው ማየቴንና ድርጊቱ አግባብ አለመሆኑን ሳልገልፅ ማለፍ አልፈልግም። ይሄው የዋጋ ንረት እያሻቀበ የሚወጣ እንጂ የሚወርድ አለመሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የአንዳንድ ምርቶች እጥረት ጭምር መኖሩም ተስተውሏል ለአብነት ያህል አሁንም ቢሆን በነዚህ በአብዛኞቹ አካባቢ በሚገኙ የእሁድ ገበያዎች የዘይት ምርት እንደልብ አይገኝም።

በአቅርቦቱ ላይ ከፍተኛ እጥረት ይታይበታል። ዱቄትም ቢሆን እንዲሁ የአቅርቦት እጥረት አለበት። ሰው በብዛት ይጠቀም የነበረው ሩዝም ቢሆን ጭራሹኑ አቅርቦቱ የለም ። የሳሙናው ዋጋም ከሰማይ ርቆ ሰው ልብሱን አጥቦ መልበስ ቀርቶ ፊቱን በሳሙና እስከመታጠብ እስከማይችል ደረጃ ደርሶ ገዝፏል።

በጥቅሉ በነዚህ በእሁድ ገበያዎች ምግብ ነክም ሆነ ምግብ ነክ ያልሆኑ ምርቶች ዋጋ በፍጥነት መጨመሩን ቀጥሏል። ሄዶ ሄዶ የጭማሪው ማቆሚያ የት እንደሆነ አይታወቅም። አሁን አሁን የእሁድ ገበያ ምርት አቅራቢዎችም እንደመደበኛው ገበያ ምርት አቅራቢዎች ሸማቹ ዋጋ ጠይቆ ይሄን ያህል የሚል ምላሽ ሲሰጡት ሲደናገጥና ራሱን ይዞ ሲጮህ ቆይ ኧረ ይሄን ያህል ሲገባ ትገዛለህ በማለት ዋጋውን ዝቅዝቅ አድርገው በመጥራት በሸማቹ ላይ መሳለቅ ሁሉ ጀምረዋል። ስላቃቸው አንድና ሁለት ኪሎ ሽንኩርት ሲጠይቅ አምስትና ሦስት እንጂ አንድና ሁለት እንደሌለ በሚነግሩት ጊዜ ያለውንም ያካትታል።

የእሁድ ገበያ ምርት አቅራቢዎች በመደበኛው ቀንና ገበያ ከሚቀርበው በሳንቲምና ሁለትና ሦስት ብር ልዩነት ምርታቸውን ማቅረባቸው ሳያንሳቸው በሸማቹ ኅብረተሰብ ላይ እንዲህ ማላገጣቸው ቢያሳዝንም ሳያስተዛዝብ የሚያልፍ አይደለም ። የእሁድ ገበያ በሸማቹ አዕምሮ ከሰርኩ ገበያ የሚለይበት ምንድነው የሚል ጥያቄ መፍጠሩ አይቀርም። ዕውነት ለመነጋገር ገበያው የኑሮ ውድነቱን ለማርገብ እና የዋጋ ንረት ለማረጋጋት እንጂ ለሸማችና ኅብረት ሥራ ማኅበራት የገበያ ዕድል ለመፍጠር ነው እንዴ የመጣው ማሰኘቱም አይቀሬ ነው። በስፋት የሚሳተፉበት ሸማች ማኅበራት መሆናቸውና በእሁድ ገበያው ሰርክ ሸቀጦቻቸውንና ምርቶቻቸውን በየራሳቸው መደብር ከሚያቀርቡበት ዋጋ በላይ በእሁድ ገበያ ሲያቀርቡ መታየታቸው ሸማቹንም ሆነ በሸማቹና በአቅራቢው መካከል ያለውን ግንኙነትና የገበያ ሁኔታ የታዘበውን ሁሉ ይሄንኑ ለማለት ይጋብዘዋል።

አሁን አዲስ አበባ ከተማ ላይ የሚታየው የዋጋ ንረት መንስኤ ብዙዎች እንደሚሉት ዋንኛ መንስኤ መንግሥትም ሆነ የመንግሥት አካል ነንና በንግዱ ጉዳይ ላይ ያገባናል የሚሉ የንግዱ አመራሮችና ነጋዴዎች እንደሚሉት የአምራች በምርት ላይ ጭማሪ ማድረግ፣ የውጪ ምንዛሪ እጥረት፣ በምንዛሪው እጥረት ምክንያት ጥሬ ዕቃ አለመኖር ፣የፍላጎትና አቅርቦት አለመመጣጠን፣ የመሠረታዊ ፍጆታዎች ፍላጎት ማደግ፣ የገንዘብ የመግዛት አቅም መዳከም በዋነኝነት መጥቀስ ይቻላል።

በአዲስ አበባ ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ አስተባባሪነት አዲስ አበባ ከተማ ላይ የዋጋ ንረትን በማርገብና ገበያ በማረጋጋት ስም ወደ እሁድ ገበያ እንዲወጡ የተደረጉት የሸማችና የተለያዩ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ቢሆኑ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገባቸው የችግሩ በአካል መሆናቸው የማይቀር እንደሆነ ይሰማኛል ።

እነዚህ የሸማችና የኅብረት ሥራ ማኅበራት የዋጋ ንረት በማርገብ ስም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አማካኝነት ወደ እሁድ ገበያ መግባታቸው አሁን ላይ ከተማ አስተዳደሩ የሚጠብቀውን ያህል ገበያን እያረጋጋ የኑሮ ውድነቱን እያረገበ መሆኑም ቢፈተሽ አይከፋም። እንዴውም በተለያየ መንገድ የዋጋ ንረቱንና የኑሮ ውድነቱን ለማባባስ የራሱን አስተዋፅዖ እያደረገ ነው። ይሄን ያልኩበት ምክንያት በአንድ በኩል እነሱ በምርትና ሸቀጥ ላይ ዋጋ በጨመሩ ቁጥር በመደበኛው ገበያ ተሰማርቶ የሚያቀርበው ነጋዴ የዛኑ ያህል እነሱን ተከትሎ የዋጋ ጭማሪ የሚያደርግበት ሁኔታ ስላለ ነው።

በሌላ በኩል ከነጋዴው ጋር በመመሳጠር የሸቀጥና ሌሎች ምርቶችን አየር በአየር በመሸጥ እጥረት እንዲፈጠር ስለሚያደርጉ ነው ። በመሆኑም ከተማ አስተዳደሩ የእሁድ ገበያን ጠንካራ ጎን ማጠናከር ደካማ ጎኑን ደግሞ መንቀስ በመንቀስ የእሁድ ገበያ በከተማችን ውጤታማ ሆኖ እንዲቀጥል ይገባዋል እላለሁ!

---


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ
- ዘላለም ግርማ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# መኀልዩ መኀልዩ ዘኢትዮጵያ ሕዝብ

**ከአሰባቸው ደሳለኝ አበሻ (ለንደን)**

ለዘመናት ፈተናዎቹን ሁሉ ተቋቁሞ ፤ ከምንም ነገር በላይ ሀገርን አስቀድሞና ህልውናዋን አስቀጥሎ ከትውልድ ወደ ትውልድ እያስተላለፈ ያለ ታላቅ ሕዝብ ሚሊየን ጊዜ ቢደነቅ ፣ ቢመሰገንና ቢወደስ ያንስበታል እንጅ አይበዛበትም ። ከጥላቻ ፣ ከልዩነት ፣ ከቂም በቀል ፣ ከሴራና ከደባ ፣ ከሀሰተኛና የተዛባ መረጃ በላይ ከፍታ ላይ ያለ ሕዝብ በቅጽል ጋጋታ ሌት ተቀን ቢሞካሽ ያንስበታል እንጅ አይበዛበትም ። ከርዕዮተ አለም ፣ ከተቋም ፣ ከሀሰተኛ ትርክት ፣ ከታሪክ ምርኮኛነት ፣ ከመደበኛና ከማህበራዊ ሚዲያ በላይ የሆነ ታላቅ ሕዝብ ምስጋናና አድናቆት ቢጎርፍለት ያንሰዋል እንጂ አይበዛበትም። ማንነትን ኢላማ አድርጎ ከተፈጸመ ጭፍጨፋ ፣ ጥቃት፣ ግጭት ፣ መፈናቀልና መዘረፍ በላይ ሆኖ በሰውነት ማማ ላይ የተቀመጠ አስተዋይና አርቆ አሳቢ የሆነ ሕዝብ ለሰዓታት ቆመው እጅ እስኪቃጠል ቢያጨበጭቡለት ያንስበታል እንጂ አይበዛበትም ።

እየተራበ ፣ እየተራዘና በድህነት እየተጎሳቀለ ለሀገሩ ህልውና ሲል በምንም የማይተመንና የማይገለጽ ውድ ዋጋ እየከፈለ ላለ ሕዝብ ቅኔ ቢቀኙለትና ቢዘፍኑለት ያንሰዋል አንጅ አይበዛበትም ። በተለይ ካለፉት አራት አመታት ወዲህ የሰሞነኛውን ጨምሮ እርስ በርሱ እንዲጋጭ ፤ ወደለየለት አመጽና ተቃውሞ እንዲገባ ሺህ ጊዜ ቢተነኮስ ፤ ሀሰተኛ መረጃ እንደ ፍላጻ ከየአቅጣጫው ቢንበለበልበት ሀገሬና አብሮነቴ ይበልጥብኛል ብሎ እርፋችሁ ተቀመጡ ያለ ልዩና ታላቅ ሕዝብ በአደባባይ ቢደነቅና ቢሸለም ያንስበትበታል እንጂ አይበዛበትም። የሚርተኞችንና ክፉዋን የሚመኙ ድሞጾችን ሳይሆን የራሱን ድምጽ የሚሰማ የሰከነ ሕዝብ በፍጥረት ሁሉ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ ቢደነቅና ቢሞካሽ ያንስበታል እንጂ አይበዛበትም ። ለዚህ ነው "መኀልዩ መኀልዩ ዘኢትዮጵያ ሕዝብ"ያልሁት ።

መኀልየ መኀልይ ዘሰሎም ከሁሉም የሚበልጥ የሰለሞን መዝሙር ማለት ነው ። የሁለት ፍቅረኛዎች ንግግር ተደርጎም ይወሰዳል ። የፍቅረኞች ንግግር በግጥም ነውና ምት ፣ ዜማ አለው ። ሰለሞን ስለ ሙሽራውና ሙሽሪት ፣ ስለፈጣሪና ስለ ቤተ ክርስቲያን የዘመራቸውን 1005 መዝሙሮችን ይመለከታል ። ሙሽራው ልዑል እግዚአብሔርን ሲወክል ሙሽራይቱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት። መኀልይ እንደ ለዘብና ወረብ አይናት በፍጥነት የሚዘመር ጥዑም ዜማ ነው ። መዝሙሮቹ በተለያየ ስልት ዜማ ቢደጋገሙም ያው ስለፈጣሪና ቤተ ክርስቲያን ክብር ፣ ቅድስና የሚመስክሩ ናቸው ። ይህ መጣጥፍ ታላቁን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚዘክር ፣ የሚያወድስና የሚያከበር ሆኖ ስለአገኘሁት " መኀልዩ መኀልዩ "ዘኢትዮጵያ ሕዝብ" ማለትን መርጫለሁ ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ታላቅነት በታላቁ መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስና በቅዱስ ቁራን ስሙ ተደጋግሞ ከመወሳት ይጀምራል ።

የሀገራችን ታሪክ ከካም ይመዘዝ ከኩሽ ወይም ከኢትዮጲስ ይሁን ከሳባ አልያም ከማክዳ ፣ ከቀዳማዊ ምኒልክ ወይም ከሳባውያን ፣ ከሀበሻ ይሁን ከአግዓዚ፣ ወዘተ . መዳረሻው ታላቅነት ነው ። የቀደምት ስልጣኔአችን እርሾ የተጣለው ተቦክቶ የተጋገረው በዚህ የታላቅነት እልፍኝ ነው ። ኢትዮጵያዊነት የተገመደበት ገመድ የተፈተለበት ቃጫ የበቀለው ከዚህ ታላቅ ምድር ነው ። የስነ ህንጻ ፣ የመርከብ ፣ የንግድ ፣ የመጀመሪያው የመገበያያ ገንዘብ ፣ የእርሻ ከፍ ሲልም የስነ መንግስት መሰረታችን የተጣለው ኢትዮጵያም የተቀለሰችው በዚሁ ምድር ነው ። ዛሬ ካስማዋ ድንኳኗ ጠቦ ጦቦ ቀይ ባህርን ሱዳንን ደቡብ አረብያን ባይሻገርም ። የዚህ ሁሉ ከፍታችን ልዕልናችን የማዕዘን ድንጋይ ኢትዮጵያዊነት ነው ።

ከእስክንድርም ይሁን ከፐቶሎሚ አልያም ከግሪክ መናገድ እንዲሁም ዲፕሎማሲ አህዱ ያልነው በታላቋ ኢትዮጵያ በአዶሊስ ነው። ቀዳሚው የግንብ ቤተ መንግስትም ባኪንግህም አልያም ኋይት ወይም ብሉ ሀውስ ሳይሆን አክሱም ነው የተገነባው ። በዩኔስኮ በቅርስነት የተመዘገቡት እስከ 33 ሜትር የሚረዝዝሙ ከአንድ ድንጋይ የተቀረፁ ሀውልቶች ፤ በቦና ጊዜ የተገነባው ምን አልባትም የመጀመሪያው የውሃ ማከፋፈያ፤ ዘብን በማቆም ንግድ መናገድ ፤ የፅሕፈት ስርዓት የተጀመረው ፤ ከሁሉም በላይ በተለይ ንጉስ አፍላስ ከሱዳን የተወሰነው ክፍል ፤ ቀይ ባህርን ተሻግሮ ደቡብ ምዕራብን ቆርሶ ከማስተዳደሩ ባሻገር የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገሥታዊ አገዛዝ መስራች እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ ። ከእሱ በኋላ የነገሱት ኢላ አሚዳ ፣ ኢዛና እና ካሌብ የአክሱምንና የኢትዮጵያን ስልጣኔ አስቀጥለዋል ። ሶስቱ አብርሀማዊ እምነቶች ክርስትና ፣ አይሁድና እስልምና ወደ ሀገራችን የገቡትም በዚሁ ዘመን በዚሁ በር ነው ።

የመጀመሪያዎቹ የመሐመድ ተከታዮች በነብያቸው ምሪት ተሰደው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ እጁን ዘርግቶ የተቀበላቸው የክርስቲያን ንጉስ ኢትዮጵያዊ ነው። የዛሬው የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት አስኳል እንበለው እራስ ወይም ዲ ኤን ኤ አልያም ልብ እንበለው የደም ስር የሚመዘዘው ከዚህ ታላቅነት ነው። በዘመናት ጅረት ፣ በትውልድ ቅብብሎሽ ፣ በአይዶሎጂ ውርክብ አያረጅም ። አይፈዝም ። አይደበዝዝም ። አይወይብም ። አይጠወልግም ። ለዚህ ነው ወጀቡን ማዕበሉን አልፎ ዛሬ ላይ የደረሰው ። ሀገርንና አብሮነትን እያስቀጠለ ያለው ።

የጥንታዊ ስልጣኔ ፋና ወጊነት ከሚገለጽባቸው አንዱ በሆነው ስነ ፈለክ ኢትዮጵያውያን ከፊተኛው ረድፍ ነበሩ ። በኪነ ህንጻና በጹሑፍም ቀዳሚ ነበሩ ። ሀገራችን ከ3ና 4ሺህ አመታት በፊት በህዋ ምርምር ዘርፍ የዛሬዎቹን ልዕለ ኃያላን ከፊት ሆና ስትመራ እንደነበር የጥንት ብራና መፅሐፍትና ስንክ ሳሮች ዋቢ ከመሆናቸው ባሻገር አለማቀፉ የአስትሮኖሚ ሕብረት በሀገራችን ልዕልት ፣ ንግስትና ንጉስ ስም ሕብረ ከዋክብት constellations መሰየሙን ስንቶቻችን ይሆን የምናውቀው !? ስለ ቀደምት ኢትዮጵያውያን የስነ - ፈለክ / የሕዋ / እውቀትና በዘመን አቆጣጠር ምን ያህል የተራቀቁ እንደነበሩ በማስረጃ የሚተነትነው የሮዳስ ታደሰና ጌትነት ፈለቀ ( ሁሉም ፒ ኤች ዲ ሰርተዋል ) ። በጋራ በደረሱት ፤ " አንድሮሜዳ " መፅሐፍ 5ኛ ዕትም ላይ ፤"... ከጥንት ጀምሮ እስከ ዛሬ ያሉ የውጭው አለም ታሪክ ፀሐፊዎች ...' ጥንታዊ ዘር ' በመባል የምትታወቀውን ኢትዮጵያን ...አውሮፓና እስያ ባልሰለጠኑበት ዘመን ...ፍልስፍና ፣ ሥነ ጽሑፍ ፣ ሒሳብ ፣ ግብርና ፣ ሕክምና ፣ የከዋክብት ጥናት ...የኢትዮጵያውያን ነባር ሀገር በቀል እውቀቶች እንደነበሩ ተናግረዋል ።... " ይህ ቀደምት ኢትዮጵያውያን ለስነ ፈለክ የማይናወጥ መሰረት እንደነበራቸው ያረጋግጣል ። የዛሬው ታላቅነቱ ሚስጥር ቋጠሮ ከዚህም ይፈታል ።

በሌላ በኩል ኢትዮጵያ የጥንት ስልጣኔ ባለቤት መሆኗን እና ለስነ - ፈለክ ምርምር ወረት ፣ መነሻ እንደነበራት የሚያረጋግጡ የቀደምት ሊቃውንት እማኝነት ከፍ ሲል በተገለፀው መፅሐፍ እንደሚከተለው ተዘግቧል ። " 60 ዓመት ቅድመ ልደት ክርስቶስ የነበረው ዲዎዶርስ ሴኩለስ የተባለ የተሪክ ሊቅ ' አውሮፓውያን ኋላ ቀር እድገት አኗኗር ላይ በነበሩበት ወቅት ኢትዮጵያ ታላቅ ስልጣኔ ላይ የነበረች ...ኢትዮጵያውያን ለግብጻውያን ስልጣኔ ያስጀመሩና እስከ ሕንድ ድረስ የገዙ ናቸው ። ' ...

በ700 ዓ ም የነበረው የቤዛንታይኑ እስቲፋንስ ባካሄደው ጥልቅ ጥናት ' ኢትዮጵያ መሬታችን ላይ የተመሰረተች የመጀመሪያ ሀገር ናት ' ሲል አርኖልድ ኸርማን ሉድዊግ የተባለ የጀርመናዊ የታሪክ ፀሐፊ ደግሞ ' ኢትዮጵያን የመሰለ ጥንታዊ ሀገር ወዴት ይገኛል !? ' ሲል ይሞግታል ፤ ከ800 ዓመት ክርስቶስ ልደት በፊት የኖረው ሆሜር ኢሊያድና እና ኦዲሴይ በተባሉ ዘመን ተሻጋሪ ስራዎቹ ኢትዮጵያውያን ' እስከ መሬት ጫፍ ድረስ የሚኖሩና ከአምላክ ጋር ቅርበት ያላቸው ' በማለት ይገልጻቸዋል ።

የታሪክ አባት በመባል የሚታወቀው ሔሮዶቶስ ኢትዮጵያውያንን ' ከሰሐራ በታች የሚኖሩ ፣ ጥቁር ቆዳ ያላቸው ...ብልሆች ፤ በዓላቶቻቸውና ሀሴታቸውም ሳይቀር አማልክትን ስለሚያስደስት የአማልክት አምላክ እየሄደ በዓላቱን በደስታ አብሯቸው ያሳልፋል ' ብሏል ። ... ዲዮዶር የተባለ የሮም ፀሐፊ ደግሞ ' ከግብፅ በፊት ስልጡንና ገናና ነበረች ። ግብፅን ቀኝ ገዝታ 18 የኢትዮጵያ ነገስታት ተፈራርቀውባታል ። ...' ይላል ።

"ሲያወጋ ውሎ ቢያድር የማይሰለቸው ደራሲ አለማየሁ ገላጋይ ( በግሌ ከብዕሩ ትዕባት ይልቅ አንደበተ ርቱዕነቱ ስለሚበልጥብኝ ፤ ተመርጎ እንደከረመ የጨፋቂት ጊዎርጊስ የገብስ ጠላ ስለሚያረካኝ " ደራሲ " የሚለውን ማዕረጉን በተሰጠኝ ስነ ፀጹሑፋዊ መብቴ poetic license " አፈ ማር " ብየዋለሁ ። ) በፍ ት ሕ መፅሔት 2ኛ አመት ቁ 60 ታህሳስ 2012 ዓም ዕትም ፤ " ከሮኬት ሮክ ወደ ሳተላይት ሀልዮት " በሚል ርዕስ ' ባወጋን ' መጣጥፉ "...ከእኛ ይልቅ አባቶቻችን ለሳተላይት ምንጠቃ የሚያበቃ የህዋ እውቀት ነበራቸው ። ህዋውን በአቅጣጫ ፣ ፕላኔቶችን በደረጃ መድበዋል። በጀት ባይኖር ትኩረት ፣ ሙከራ ባያደርጉ ሃልዮት ነበራቸው። ሰማየ ሰማያትን እግዜአብሔርን ባማከለ ዕውቀት ( Theocentric ) ለሰባት ከፍለው አንብረዋል ።

ሰባቱ ዓለማት ( ሰማያት ) መንበረ መንግስታት ፣ ፅርሃ አርያም ፣ ሰማየ ውድድ ፣ ኢዮሪያሌም ሰማያት ፣ ኢዮር ፣ ራማ እና ኤረር ብለው ከፋፍለው አጥንተዋል። ..." ብሎናል ። ሀገራችን የጥንታዊ ስልጣኔ ባለቤት መሆኗን በአደባባይ ካስመሰከረ በኋላ በአለማቀፉ የአስትሮኖሚ ሕብረት የተሰጣትን ቦታ ይተነትናል ። "... ሕብረ ከዋክብት constellations ማለት በሰማይ ላይ የሆነ አይነት ቅርፅ የሚሰራ የከዋክብት ስብስብ ሲሆን ቅርጹም ከማይቶሎጂ ጋር በተያያዘ መልኩ የሰው ፣ የእንስሳት ወይም ሕይወት የሌለው ነገር ሆኖ ሊገለጽ ይችላል ።...አለማቀፉ የአስትሮኖሚ ሕብረት በ1930 ዓም ከ88 ሕብራተ ከዋክብት ውስጥ ሶስቱን ማለትም አንድሮሜዳን፣ ካሲዮፒያንና ሴፌውስን በኢትዮጵያውያን ስም መዝግቧል ። ... አንድሮሜዳ የኢትዮጵያ ልዕልት ስትሆን ፤ ካሲዮፒያን ደግሞ የኢትዮጵያ ንግስት ናት ። ሴፌውስ ደግሞ የኢትዮጵያ ንጉስ ነው ። ..."

በአለት ላይ ስለተመሠረተው የኢትዮጵያ ሕዝብ የኋላ መነሻ ይሄን ያህል ካልሁ ፤ ይሄን ታላቅ ሕዝብ የማመሰግንበትና የማወድስበት ሚሊዮን ምክንያቶች ቢኖሩኝም ሰሞነኛ መግፍኤዎችን እመለስባቸዋለሁ ። ከዚያ በፊት ግን ይቺ ሀገር ከ3ሺህ በላይ አመታትን ነጻነቷን፣ ሉዓላዊነቷንና የግዛት አንድነቷን አስከብራና አስጠብቃ ያስቀጠለችው በሀገረ መንግስቷ ፣ በአገዛዟ፣ በተቋማቷ ፣ በመሪዎቿ ሳይሆን በታላቁና ንኡዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ። እንደ ሀገር የገጠሙን ፈተናዎችና ቀውሶች እንደዛሬው ሀገረ መንግስትን ፣ ተቋማትን ፣ መሪዎችንና ልሒቃንን ተሻግረው ከአንዴም ሁለት ሶስት ጊዜ ...ሊያንበረክኩንና ሊረቱን ሳለ የመጨረሻ ምሽግ ሆኖ የታደገን ፤ ወደፊትም የሚታደገን ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስለመሆኑ ቅንጣት ታክል ስለማልጠራጠር ነው፤ ያለምንም ስስትና ንፍገት ታላቁን የኢትዮጵያን ሕዝብ"መኀልዩ መኀልዩ ዘኢትዮጵያ ሕዝብ ፤"ስል መወድስ የያዝሁለት።

የቀደመውን እናቆየውና ከ66ቱ አብዮት ከነጭና ቀይ ሽብር ማዕት ፤ ከ17ቱ አመታት ዘግናኝ ደም አፋሳሽ የእርስ በርስ ጦርነት ፤ ለግማሽ ክፍለ ዘመን ያህል መዋቅራዊና ተቋማዊ ሆኖ ከተለፈፈውና ከተሰበከው ልዩነት ፣ ጥላቻ ፣ ዘረኝነት ፣ ቂም በቀል ፣ ወዘተረፈ፤ ህወሀት ከሽግግር መንግስቱ አንስቶ ከአገዛዝ እስከተፈነገለባቸው አመታት ንጹሐን በመላው የሀገሪቱ ክፍል በማንነቱ እንዲጠቃና እንዲጨፈጨፍ አድርጓል። በምስራቅ ሐረርጌ በጋራ ሙለታ ፣ በወተር ፣ በበደኖና በድሬደዋ ፤ በምዕራብ ሀረርጌ በገለምሶ ፤ በአሰቦት ገዳም፣ በአርሲ ፣ በአርባ ጉጉ ፣ በአጋሮ ፣ በሸቤ ፣ በጉራ_ ፈርዳ ፣ በወለጋ ፣ በኖኖ ፣ በአማያ ፣ በቤኒሻንጉል ጉምዝ፣ በከማሺ ፣ በመተከል ፣ በአፋር እና በራሱ ክልል ዘርፈ ብዙ ጥቃት እንዲፈጸም አድርጓል ።

በዚህ የተነሳም ከፍ ብዬ እንደገለፅሁት በበዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ተገድለዋል ፣ አካለ ጎደሎ ሆነዋል ፣ ተፈናቅለዋል ፣ ተዘርፈዋል ። በሱማሌ ክልል በተለይ በጅግጅጋ ፤ የአርቲስተት ሀጫሉን ግድያ ተከትሎ በኦሮሚያ የተፈጸሙ ጭፍጨፋዎች ፤ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ፤ በዩኒቨርሲቲዎች ይቀሰቀሱ የነበሩ ማንነትን ኢላማ ያደረጉ ግጭቶችም ሆኑ በሌሎች አካባቢዎች የተፈጸሙ ግፎች ሆኑ ከፍ ብለው የተፈጸሙ ኀልቆ መሳፍርት የሌላቸው ሰቆቃዎች ግብ ሀገሪቱን እንደ ሩዋንዳ ወደለየለት የእርስ በርስ ግጭት ፣ ዘር ማጥፋት መዝፈቅና ሀገሪቱን መበተንና ማፍረስ ነው ። ሆኖም ይህ እኩይ ሴራ በጥበበኛው ፣ በአስተዋዩ ፣ በአርቆ አሳቢውና በታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ መክኗል ። ከሽፏል ።

የእናት ጡት ነካሾች እንዲሁም ጋላቢዎቻቸውና ታሪካዊ ጠላቶቻችን ግን እስከመጨረሻዋ ህቅታቸው አልተኙልንም። ባለፉት አራት አመታት ህወሀት በተላላኪዎቹ አማካኝነት በመላ ሀገሪቱ እስፖንሰር እያደረገና ስምሪት እየሰጠ የቀፈቀፉቸው በሺዎች የሚቆጠሩ ጭፍጨፋዎችና ቀውሶች በዚህ ታላቅ ሕዝብ አስተዋይነት ቢከሽፍበት የመጨረሻ ካርዱን መዘዘ ። በሸረበሁት ሴራ ሀገሪቱ የማትፈርስ የማትበተን ከሆነ እራሴ አፈርሳታለሁ ብሎ ከቡችሎቹና ከጋላቢዎቹ ጋር አብሮና ተማምሎ ተነሳ ። ሰሜን ዕዝን በማጥቃት ጦርነት አወጀ። የአማራንና የትግራይ ሕዝብን ለማቆራረጥ በማይካድራ የዘር ማጥፋት ወንጀል ፈጸመ ።

ሶስት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ድባቅ ቢመታም አፈር ልሶ በመነሳት ፤ በአማራና በአፋር ክልሎች ተነግሮና ተሰምቶ የማያልቅ ሰቆቃ ፣ ግፍ ፣ ዘረፋና ውድመት ፈጸመ ። በጋሊኮማ ፣ በአጋምሳና በሌሎች አካባቢዎች የተቀነባበረና የታቀደ የዘር ማጥፋት በመፈጸም ሕዝብ በሕዝብ ላይ እንዲነሳ አሴረ ። ሸኔንና ሌሎች ተላላኪዎቹን በመጠቀም የእርስ በርስ ግጭት ለመቀስቀስ ለማየት የሚዘገንን ለመስማት የሚሰቀጥጥ ግፍ እያስፈጸመ ቢሆንም ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን እንደ ትላንቱ የሀገሩን ህልውና ማስቀጠልና አብሮነትን መርጧል ።

**መኀልዩ መኀልዩ ዘኢትዮጵያ ሕዝብ !**

**አሜን።**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የሥራ ፈጠራ ሀሳብን ወደ ተግባር የመለወጥ ጅማሮ

ዳግም ከበደ

ከትምህርት መስፋፋትና ከመሳሰሉት ጋር በተያያዘ በየአመቱ በርካታ ወጣቶች የስራውን አለም ለመቀላቀል ይደርሳሉ። የስራ እድል አስመልክቶ ያለው አመለካከት አሁንም የመንግስትን እጅ ከመጠበቅ ጋር የተያያዘ መሆኑን ተከትሎ በተለይ ወጣቶች የስራ እድል ጥያቄን ሲያነሱ ይስተዋላል። ስራ መፍጠር ብዙም የተሄደበት አይደለም።

ጉዳዩ ትልቅ ነውናም መንግስት ትኩረት ሰጥቶ ከሚሰራባቸው ተግባሮች መካከል ለዜጎች የስራ እድል መፍጠርን አንዱ ስራው አርጎ እየተንቀሳቀሰ ነው። መንግስት ለሀገሪቱ ወጣቶች ሁሉ የስራ እድል አመቻችቶ ተቀጣሪ ማድረግ ይችላል ተብሎ ባይታሰብም፣ በዋና ዋና ዘርፎች ላይ ዜጎች ተሰማርተው እንዲያገለግሉ የማድረግ ታላቅ ሃላፊነት ያለበት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የእቅዶቹ ሁሉ አካል አርጎ እየሰራ ነው።

ዜጎች መንግስት ከሚያመቻቸውና የስራ እድል ባሻገር የራሳቸውን ስራ ፈጥረው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላትና የስራ አጥ ቁጥርን ለመቀነስ ከፍተኛ ድርሻ ያለባቸው ቢሆንም፣ ከስልጠና፣ ከፋይናንስ ድጋፍና ከመሳሰሉት ጋር ተያይዞ የዜጎች በራሳቸው የስራ እድል የመፍጠር ሁኔታ የሚጠበቀውን ያህል አይደለም። በዚህ በኩል መንግስት ድጋፍ እያደረገ ቢሆንም፣ የግሉ ዘርፍ ሚናውን እየተወጣ አይደለም።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው ውስጥ የመሪነት ሚና እንዲወስድ በመንግስት ፖሊሲ ተቀርጾው ማበረታቻዎች እየተደረጉ ይገኛሉ። ዘርፉ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ዘርፍ ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው ለማድረግ መንግስት እየደገፈ መሆኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ አንዱ ግብ ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና ገቢን መጨመር እንዲሁም የስራ እድል መፍጠር እንደ መሆኑ በዚህ ረገድ የግሉ ዘርፍ ሰፊውን ድርሻ መውሰድ እንደሚኖርበት በመንግስት በኩል ታምኖበታል። በ2014 ተሻሽሎ የወጣው ይህ ማሻሻያ የግሉን ዘርፍ የመሪነት ሚና ማረጋገጥ ዋነኛ ተግባሩ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ። በተደጋጋሚ የሚገለጽለት የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ግብን ለመተግበርም የግሉ ዘርፍ ዋንኛ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው።

የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እየጨመረ እንዲሁም የሚያስገኘው የስራ እድል በዚያው ልክ እየጨመረ ቢመጣም፣ አዳዲስ የፈጠራ ስራዎችን ከመደገፍና ለዜጎችም ለባለሀብቱም ለሀገርም እንዲጠቅሙ በማድረግ በኩል ውስንነት እንዳለበት ይገለጻል።

በኢትዮጵያ ሰፊ የስራ እድል የሚፈጥሩ የፈጠራ ሃሳቦች ያላቸው ግለሰቦች በርካታ ናቸው። በተለይ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፉ ደግሞ ብዙ ያልተነካ እምቅ አቅም ያለው እንደሆነ ይታመናል። ይሁን እንጂ በዚህ ሰፊ የስራ እድል እንደሚፈጥር ተስፋ በተጣለበት ዘርፍ ላይ የሚሰማሩ የግል ባለሃብቶችም ሆኑ ተቋማት ያላቸው ፍላጎት ደካማ እንደሆነ ይነገራል። በተለይ በግል ተነሳሽነት የቴክኖሎጂ የፈጠራ ስራ ሰርተው ለራሳቸውም ሆነ ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል ለመፍጠር የሚያስችል አቅም ያላቸው ወጣቶች የሚደግፋቸው የግል ባለሃብትም ሆነ መሰል ድርጅት ባለማግኘታቸው ባክነው የሚቀሩበትና ከመንግስት እጅ ስራ የሚጠብቁበት አጋጣሚ በስፋት ይስተዋላል።

አሁን አሁን ይህን ችግር የሚቀርፍ መፍትሄ አመላካች መረጃዎች እየሰማን እንገኛለን። በመንግስት መዋቅር ውስጥ የሚገኘው የስራ እድል ፈጠራና ክህሎት ሚኒስቴርም ሆነ በክልል በቢሮ ደረጃ ያሉ ተመሳሳይ መዋቅሮች ዜጎች ከመንግስት ስራ ከሚጠብቁ ይልቅ ክህሎታቸውን አሳድገውና የፈጠራ ብቃታቸውን ተጠቅመው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዘርፍ መልካም ውጤት እንዲያመጡ የግል ዘርፉን የማነቃቃትና በፖሊሲ በመደገፍ ለማበረታታት እየሰሩ ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱ የፈጠራ ባለሙያዎችንና ባለሃብቶችን እንዲሁም ባንኮችን የማስተሳሰር ስራ ነው።

የዝግጅት ክፍላችን በቅርቡ በኦሮሚያ ክልል የስራ እድል ፈጠራና ክህሎት ቢሮ ባዘጋጀው "ሶስተኛው የቴክኖሎጂና ፈጠራ ክህሎት" ውድድር ላይ ተገኝቶ ይህንን ተገንዝቧል። ከዚህ ባሻገር የግል ባለሃብቶች የስራና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ስራ ያላቸው ወጣቶችን የሚደግፉበትና በዚህ ስራ የግሉ ዘርፍ አበርክቶ ጎልቶ የሚወጣበትን መንገድ ለማመቻቸት የሚደረገውን ጥረትም ለመመልከት ችሏል።



አቶ አለሙ ዘለቀ

ከዚህ ውስጥ ለዛሬ አምዳችን አንድ በግል ባለሃብቶች ጥምረት ከተመሰረተና የወጣት የፈጠራ ባለሙያዎችን ሃሳብ ወደ ተግባር ለመለወጥ ድጋፍ ከሚያደርግ የኢንተርፕረነርስ አሶሲዬሽን ጋር ቆይታ አድርገናል። አቶ አለሙ ዘለቀ ይባላሉ። ዋነኛ ትኩረቱን የስራና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ባለሙያዎችን የመደገፍና የማብቃት ስራ ላይ ትኩረቱን ያደረገው የሸገር ኢንተርፕረነርስ ማህበር (አሶስዬሽን) ዋና ስራ አስፈፃሚ ናቸው።

የማህበሩ ዋንኛ ፍልስፍና "በኢትዮጵያ ውስጥ ዜጎች ሃብት የሚያፈሩበት መንገድ በእውቀት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ኢኮኖሚው ማደግ ቢችልም እንኳ በዋናነት መፈታት ያለባቸው ማህበራዊ ችግሮች አይፈቱም። ስለዚህ ምን መደረግ አለበት?" የሚል ሃሳብ አንሸራሽሮ የመፍትሄ ሃሳብ የሚጠቁም መሆኑን ዋና ስራ አስፈጻሚው ያብራራሉ። ኢኮኖሚው በተከታታይ ማደጉን ጠቅሰው፣ ለዜጎች ግን በቂ የስራ እድል የፈጠረ አለመሆኑን ያመለክታሉ። ይህ የሆነው የሃብት ማፍራት አካሄዱ እውቀት ላይ የተመሰረተ ባለመሆኑ ነው ይላሉ።

"ከላይ ያነሳነውን ዳሰሳ ወይም ፍልስፍናዊ እይታ እንደ መነሻ በማድረግ ለመፍትሄው አራት ዋና ዋና ነገሮች ላይ እየሰራን እንገኛለን" የሚሉት ዋና ስራ አስፈፃሚው አቶ አለሙ ይገልጻሉ። በመጀመሪያው ዜጎች በቴክኖሎጂና መሰል የፈጠራ ስራዎች ላይ ብቃት እንዲኖራቸው የሚያስችል የሙያ ስልጠና እንደሚሰጣው ይናገራሉ። ከዚያ ባለፈ ማንኛውም ግለሰብ ለማህበረሰቡ በቂ የስራ እድል የሚፈጥር ሃሳብ ካለው ያንን በምን መልኩ ወደ መሬት አውርዶ እሴት መጨመር እንደሚቻል በስልጠናው ውስጥ እንደሚካተትና በማህበሩ ለተፈፃሚነቱ ድጋፍ እንደሚደረግለት ያስረዳሉ።

እንደ አሶሴሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ገለፃ፣ በሁለተኛ ደረጃ ተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ ነው። ይሁን እንጂ በዋናነት ለኢንተርፕረነር አሊያም ለስራ እድል ፈጠራና ለቴክኖሎጂ ባለሙያ ገንዘብ ቀዳሚው ጉዳይ እንዳልሆነ ማህበሩ ያምናል።

‹‹በኢንተርፕረነር ህይወት ውስጥ ገንዘብ ወሳኝ አይደለም። ግን ደግሞ አስፈላጊ ነው" የሚሉት አቶ አለሙ፤ ወሳኙ ነገር የሰው ልጅ ያለው ክህሎትና የመፍጠር አቅሙን ተጠ ቅሞ ለመወዳደር የሚያስችል ቁመና ላይ መገኘቱ ነው ይላሉ። ይህ ሁሉ በቅድሚያ ከተሟላ በኋላና ገንዘብ የግድ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ወቅት ራእዩን እና ለአገርና ለወገን መልካም እድል ይዞ የመጣውን ሃሳቡን እውን ማድረግ እንዲችል የሸገር ኢንተርፕረነር አሶሲዬሽን ድጋፍ እንደሚያደርግ ይገልፃሉ።

አሶሴሽኑ ይህን ፍልስፍና ተከትሎ ለቴክኖሎጂና አዲስ ሃሳብ መፈጠር ምክንያት ለሚሆኑ ወጣትና ታዳጊዎች ድጋፍ እንደሚያደርግ ጠቅሰው፣ ይህን የሚያደርግበትን ምክንያት ሲያስረዱም "ገንዘብ ኖሮት ምንም ሃሳብ ሳይኖረው የሚቀር እንደመኖሩ ሁላ ምንም ገንዘብ ሳይኖረው ግን ለአገር የሚጠቅም ሃሳብ ላይ ብዙ የሚተጋ ስላለ ያንን እድል ለመፍጠር በማሰብ ነው" በማለት ምላሻቸውን ይሰጣሉ። እነርሱም ይህንን ባረጋገጡና ለዜጎች ተጨማሪ እሴት እንደሚሆን ሲታወቅ የፈጠራ ባለሙያው የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኝ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር እንደሚሰራ ይናገራሉ።

" የአሶስዬሽኑ ሁለተኛ አላማ የፋይናንስ ድጋፍ ከማድረጋችን በፊት ሁሉንም አይነት ስልጠናና የማጣራት ስራ በቅድሚያ እንሰራለን" የሚሉት አቶ አለሙ፣ በቁጥር ይህ ነው ብለው ባያስቀምጡትም መሰል ድጋፍ ያተደረገላቸው ኢንተርፕረነሮች መኖራቸውን ይናገራሉ። ከዚህ ባሻገር በመጀመሪያው ግብ ላይ በተቀመጠው መስፈርት መሰረትም ተቋሙን ከተመሰረተበት ከዛሬ ሶስት ዓመት ጀምሮ እስካሁን ድረስ 3ሺህ 700 ለሚደርሱ የቴክኖሎጂ፣ የሳይንስ፣ የዲጂታልና መሰል መስኮች ላይ የፈጠራ ሃሳብ ላላቸው ግለሰቦች አሶሴሽኑ ስልጠና መስጠቱን ይናገራሉ።

"በሶስተኛ ደረጃ እንደ ግብ አስቀምጠን የምንሰራው የገበያ ትስስር መፍጠር ላይ ነው" የሚሉት ዋና ስራ አስፈፃሚው፤ ይህን ለማድረግና በሙሉ አቅም ለመስራት የወተወሰነበት ምክንያት በሳይንስ ቴክኖሎጂና ሌሎች መሰል መስኮች ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕረነሮች የሙያና መሰል ክህሎት ኖሯቸው ምርት ቢኖራቸውም "እንዴትና የት" ማስተዋወቅም ሆነ መሸጥ ስለሚቸገሩ መሆኑን ይገልፃሉ።

ይህን ችግር አሶሴሽኑ በመረዳቱ በተለይ ወጣቶች ምርቶቻቸውንና የፈጠራ ሃሳቦቻቸውን በምን መልኩ ወደ ገበያ ማውጣት እንደሚችሉ እናሳያቸዋለን ይላሉ። በዚህ መንገድም የገበያ ትስስር በመፍጠር ኢኮኖሚው ዘላቂ፣ በእውቀት ላይ የተመሰረተና ለብዙዎች የስራ እድል የሚፈጥር እንዲሆን እንሰራለን ሲሉ ያብራራሉ።

"የገበያ ትስስር ከመፍጠር ባለፈ ከገዥዎች ጋር ያላቸው ግንኙነት እንዲዳብር እገዛ እናደርጋለን" የሚሉት አቶ አለሙ፤ ለምሳሌ ያህል የተፈጥሮ ማዳበሪያ ላይ የሚሰሩ የፈጠራ ባለሙያዎች ገበያቸውን በስፋት ለማህበረሰቡ ለማቅረብ የዋጋ ውድነት ቢፈትናቸውም ያንን መቋቋም እንዲችሉ ዘዴ በመቀየስ ልዩ ልዩ ስራዎችን መስራት እንዲችሉ ዘዴ በመቀየስ እንደሚሰራ ነው የሚያብራሩት። ለምሳሌ ያህልም በተፈጥሮ ማዳበሪያ የሚመረት አትክልትና ፍራፍሬ ሁሉም ዜጎች ገበያ ላይ ከፍ ያለ ወጪ አውጥተው መግዛት ባይችሉ ምርቱ ከገበያ እንዳይወጣ በቀጥታ የመግዛት አቅም ካላቸው ጋር ስራ ፈጣሪው እንዲገናኝና እንዲበረታታ የማድረግ ሃላፊነት ወስዶ እንደሚሰራም ያስረዳሉ።

ዋና ስራ አስፈፃሚው ከማህበሩ ዋና ዋና ግቦች ውስጥ አንዱና የመጨረሻ የሆነው ተግባር ጥናትና ምርምር መስራት መሆኑን ይገልፃሉ። በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ውስጥ ዘርፈ ብዙ ችግሮች መኖራቸውን ጠቁመው፣ በተለይ በክህሎትና ስራ ፈጠራ ላይ በእውቀት ላይ በመመስረት ብዙ ስራዎች መሰራት እንደሚቀር ይገልፃሉ።አገሪቱ በዋናነት የሰው ሃይል ቢኖራትም የአለመቀጠር ችግር በስፋት ይታያል በማለትም ይህንን ያመጣው በቂ የሙያ እውቀት አለመኖሩ መሆኑን ይገልፃሉ።

እንደ ዋና ስራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ የሰለጠኑት አገራት በብቁና ጥቂት የሰው ሃይል የዓለምን ትልቁን ኢኖኮሚ መገንባት ችለዋል። ይህን ያደረጉት ደግሞ ለኢንተርፕረነሮች ምቹ አጋጣሚን በመፍጠራቸውና በእውቀት ላይ በመመስረታቸው ነው። በኢትዮጵያም ይህ እንዲፈጠር ዋና ዋና ችግሮችን ነቅሶ መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል።

እርሳቸው የሚመሩት አሶሴሽንም በጥናትና ምርምር ዘርፉ ላይ መዋእለ ንዋይ በማፍሰስና ምሁራንን በማሳተፍ ዋንኛ ማነቆዎች በሳይንሳዊ መንገድ የሚፈቱበትን መንገድ ለመጠቆም እየሰራ መሆኑን ይገልፃሉ። ይህን የጥናትና ምርምር ውጤትም ማህበሩ ለፖሊሲ አውጪዎችና በመንግስት ለሚመለከታቸው አካላት እንደሚያቀርብም ይናገራሉ።

የኦሮሚያ የስራ እድል ፈጠራና ክህሎት ቢሮ ለሶስተኛ ጊዜ ባዘጋጀው "የቴክኖሎጂና ክህሎት ውድድር" ላይ የሸገር ኢንተርፕረነርስ አሶሲየሽን ተሳታፊ ነበር። የስራ እድል መፍጠር የሚችሉ፣ የማህበረሰቡን ችግሮች የሚፈቱ ፣ በቴክኖሎጂና ሳይንሳዊ ጉዳዮች ላይ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦች ያሏቸው ወጣቶችን የተቋሙን ድጋፍ እንዲያገኙ እየሰሩ መሆኑን ዋና ስራ አስፈፃሚው ነግረውናል። የእነዚህ የፈጠራ ባለሙያዎች ሃሳብና ስራ ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍና ለአገር እድገት የሚጠቅም ከሆነ ማህበሩ በተለያየ መንገድ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑንም አረጋግጠውልናል።

"የቴክኖሎጂና የስራ ፈጠራ ክህሎት ያላቸው ወጣቶች ከዋናው ችሎታቸው በተጨማሪ ልዩ ልዩ ብቃቶችን ማዳበር ይኖርባቸዋል" ሲሉ የኦሮሚያ ስራ እድል ፈጠራና ክህሎት ቢሮ ምክትል ሃላፊ አቶ አደም ከማል ይገልጻሉ። በተለይ የሰሩትን ቴክኖሎጂ በምን መልክ ወደ ገበያ ማውጣትና አቅም መፍጠር እንዳለባቸው፣ ራሳቸውን እንዴት ማስተዋወቅ እንደሚችሉና የግንኙነት አድማሳቸውን ማስፋት እንደሚኖርባቸው ክህሎቱ ሊኖራቸው ይገባል ይላሉ። ለዚህ ደግሞ የኦሮሚያ የስራ እድል ፈጠራና ክህሎት ቢሮ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ይገልፃሉ።

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ እንደ ሸገር ኢንተርፕረነሮች ማህበር ያሉት በግል ባለሃብቶች ጥምረት ለተመሰረቱ ተቋማት የማህበረሰቡን ችግር የሚፈቱ ቴክኖሎጂዎችን ከሚፈጥሩ ወጣቶችና ታዳጊዎች ጋር እንዲገናኙ ቢሮው ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ይህ ብቻ ሳይሆን እንደ ስንቄ ባንክ ካሉ የፋይናንስ ተቋማት ጋር ትስስር እንዲፈጥሩና ለስራዎቻቸው የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኙ ድልድይ በመሆን ይሰራል።

## ወቅታዊ ትንታኔ

# የዋጋ ግሽበቱ ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆን

**አስቴር ኤልያስ**

ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ የመስከረም ወር 2014 ዓ.ም አጠቃላይ የዋጋ ግሽበት 34 ነጥብ 8 በመቶ መድረሱን በሪፖርቱ ይፋ ማድረጉ ይታወቃል። ከጊዜ ወደጊዜ እያሻቀበ የመጣው ይህ የዋጋ ግሽበት ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ አገሪቱን እንዳይፈትን ደግሞ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው መፍትሄ እንዳለ ይናገራሉ።

ከዋጋ ግሽበቱ ጋር ተያይዞ አዲስ ዘመን ያነጋገራቸው የምጣኔ ሀብት ባለሙያውና የኦሮ-ፍሬሽ አትክልትና ንግድ አክሲዮን ማህበር ሥራ አስኪያጅ ዶክተር አደሬ አሰፋ እንደሚናገሩት፣ የዋጋ ግሽበት ማለት የምንገዛበት ዋጋ መጨመር ነው። የዋጋ ግሽበት ምን ይመስላል የሚለውን ባደጉ አገራት እና እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ያላደጉ አገራት ብሎ መክፈል ይቻላል።

ባደጉ አገራት የዋጋ ግሽበትን የሚያመላክቱ ብዙ የሚታዩ ነገሮች ቢኖሩም አቅርቦትንና ፍላጎትን ብቻ በማወዳደር እየሔደ ያለው ወዴት ነው? ያለውስ ነገር ምንድን ነው በማለት መለየት ይቻላል። ብዙውን ጊዜ የዋጋ ግሽበት የሚኖረው ፍላጎት ከአቅርቦት ሲበልጥ ነው። ይህ በእኛም አገር አንዱ ችግር ነው። ፍላጎት ደግሞ ከአቅርቦት ያነሰ ከሆነ እሱም የሚፈለግ አይደለም። የሚሸጥበት ዋጋ ከተመረተበት ዋጋ ካነሰ በራሱ ለዋጋ ግሽበት በምክንያነት የሚጠቀስ ነው። ጥሩ የሚሆነው አቅርቦቱና ፍላጎቱ ሚዛናዊ የሆነ ስርዓትን ይዞ መቀጠል ሲችል ነው።

ይህ ግን አቅርቦትንና ፍላጎትን እያወዳደሩ የዋጋ ግሽበቱን ያመጣው ምንድን ነው የሚለውን ለማወቅ ባደጉ አገራት የሚጠቀሙት መንገድ የምርት ሂደቱን፣ የግንባታዎች ወቅታዊ ሁኔታ እንዲሁም የኋሊዮሹንና የወደፊቱን በማወዳደር ነው።

ነገር ግን እንደ እኛ አገር ያሉ ያላደጉ አገራት ላይ ከዚህ ውጭ ብዙ ግምት ውስጥ የሚገቡ ነገሮች ይኖራሉ ይላሉ ዶክተር አደሬ፣ ለምሳሌ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገራት ላይ ያለው የኢኮኖሚ ሁኔታ ያልተረጋጋ ነው። ግብርናችን በጣም ኋላቀር ነው። ያሉን መዋቅሮችም ሆኑ ተቋማት ጠንካራ አይደሉም። በየጊዜው ጦርነቶች፣ ሰላም ማጣቶች እንዲሁም የፖለቲካ አለመረጋጋት የእኛ የዕለትተዕለት ኑሮ በሚመስል አይነት ሁኔታ እየታየ ነው። የውጭ ምንዛሪ ችግር፣ የመንገድ ችግር፣ የቴሌኮሙኒኬሽን ችግር፣ በዝናብ ላይ የተንጠለጠለ እርሻ ፣ አንድ ጊዜ በዝናብ አንድ ጊዜ ደግሞ በድርቅ የምንመታ እንደመሆናችን እነዚህ እነዚህ ነገሮች ግምት ውስጥ ሳይገቡ ስለዋጋ ግሽበት ማውራት አይሆንም ማለት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

በኛ ሀገር የዋጋ ግሽበትን ያመጡት ምንድናቸው የሚለውን ለመናገር የተጠቀሱት ችግሮች መነሻ ምንድን ነው? ለምንድን ነው የኖሩት? እነዚህ ችግሮች ደግሞ የዋጋ ግሽበትን ያመጡት እንዴት ነው?ለምሳሌ የዋጋ ግሽበቱ በሁሉም አይነት ምርት ላይ ላይሆን ይችላል። አንዱ ዘንድ ሲከሰት ኢኮኖሚውን እንዴት ነው አንቆ የሚይዘው? የሚለውን ነገር በደንብ ማጥናት እና መተንተን እንደሚያስፈልግ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ያስረዳሉ።

የዋጋ ግሽበቱ እንዲኖር ከሚያደርጉ የመጀመሪያ የአቅርቦትና የፍላጎት አለመመጣጠን ነው ።ይህም ገበያው እንዲሸበር ያደርጋል። ጭማሪ በመኖሩ በገበያው ላይ በድንገት የሚመጣ ፍርሃት ይፈጠራል። እኛም አገር ውስጥ እንደእነዚህ አይነት ሁኔታዎች ታይተዋል፤ እየታዩም ነው ።

ሁለተኛው ደግሞ የግብዓቶች ዋጋ መጨመር ነው። ከዓለም የምግብና የነዳጅ ዋጋ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የግብዓት ዋጋ መጨመር የሚያመጡት ምክንያቶች ናቸው። ለምሳሌ በእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ የዛሬ 16 እና 17 ዓመት ወደኋላ ተመልሰን ብናይ አንድ በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ ሰው የወር ደመወዙ ከአንድ ሺ ብር በታች ነበር። በዚያ ብር የቤት ኪራዩን ከፍሎ፣ ቤተሰቡን አስተዳድሮ በአግባቡ ይኖር ነበር። ምናልባትም እንደየሰው የሚለያይ ቢሆንም ይቆጥብ ነበር።

> ምሳሌ መንግሥት ቢሮዎችን ወደ አንድ የማምጣት፤ በውጭ አገር ያሉ አንዳንድ ቆንስላ ጽህፈት ቤቶችን እንደየአስፈላጊነታቸው በከፊል የመቀነስ ነገር ሲያደርግ ወጪዎችን እንደመቀነስ ነው፤ ወጪ ሲቀነስ የትኩረት አቅጣጫው የዋጋ ግሽበቱን ወደማረጋጋት ማስኬድ ነው

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት አዲስ ምሩቅ ወደሥራ በሚገባበት ጊዜ የደመወዙን ከፍ ማለት እያስተዋልን ነው። መሬት ላይ ያለውስ ሁኔታ ምንድን ነው ሲባል ልክ የዛሬ 16 እና 17 ዓመት ሲደረግ እንደነበረው አይነት ኑሮ ሰራተኛው ይኖራል። ይህን ያመጣው የዋጋ ግሽበቱ ነው እንጂ የወር ደመወዙ ከዛሬ 16 እና 17 ዓመት በፊት ከነበረው ጋር ሲተያይ በብዙ ጨምሯል። ይህ እንዴት መጣ ሲባል የሰው ጉልበትም ደመወዝም ሲጨምር ዋጋም በዛው ልክ ነው መጨመር ያለበት ይላሉ።

ሌላው ትርፍ ከማግበስበስ የመጣ ነው፤ሰዎች የሚነግዱ ከሆነና ንግድ መኖር ካለበት ማትረፍ መቻል አለባቸው። ነገር ግን ከእኛ አገር ነባራዊ ሁኔታ ጋር አያይዘን የምናይ ከሆነ ስግብግብነት ይጨመርበታል። በአቋራጭ በቶሎ ለመበልጸግ የሚደረግ ሩጫ ይስተዋላል።ማለትም ከሌሎቹ ነጥቆ የመበልጸግ ፍላጎት አሁንም የዋጋ ግሽበቱን ከቁጥጥር ውጭ እንዲሆን አድርጎታል።

በሌላ በኩል ደግሞ እኛ አገር በደንብ አለ ብዬ የማስበው፤ሰዎች በእጃቸው ላይ ያለውን እቃ ለመሸጥ ብሎም ገበያ ለመሳብ ነው ጥረት የሚያደርጉት። በእርግጥም ንግድ መሆን ያለበት እንደእርሱ ነው። ከብዙ ሽያጭ ትንንሽ ትርፎችን እያገኙ ብዙ ትርፍ ነው ማግኘት ያለባቸው። አሁን ግን ሰዎች ለመሸጥ እንኳ እምብዛም አይጨነቁም። በተለይ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚችል አይነት እቃ ከሆነ ብዙ ለመሸጥ አይጨነቁም። ምክንያቱም በአዕምሯቸው ውስጥ ይጨምራል የሚል ግምት አላቸውና ነው። ችግር የለም፤ ይቀመጥ፤ ነገ ይጨምራል የሚል አካሄድ ደግሞ በጣም አደገኛ ነው።

እንደዚህ አይነት አካሄድ ወደባህልነት እየተሸጋገረ ነው፤ ለምሳሌ አንድ እቃ ማታ ከተገዛበት ሱቅ ጠዋት በዛው ዋጋ ለመግዛት ሲጠየቅና ዋጋው ጨመረ ሲባል ምንም የሚሰማን እንግዳ ነገር አይኖርም፤ ጨመረ ደግሞ ብለን ነው የምንገዛው። ምክንያቱም በሰው አዕምሮ ውስጥ ይጨምራል የሚል ግምት ስለነገሰ ነው። በየትኛውም መልኩ የሚባለው ይቀመጥ ይጨምራል ነው፤ ለምን እንደሚጨምርና እንዴት እንደሚጨምር ለማብራራት እንኳ ጊዜ የሚሰጥ የለም ሲሉ ይናገራሉ።ሸማቹ ማህበረሰብም አምኖ የተቀበለው ጉዳይ በመሆኑ ለምን ብሎ አይጠይቅም።በመሆኑም ይህ ሁኔታ የዋጋ ግሽበትን አምጥቷል።

ሌላው ከበቂ በላይ ገንዘብ ወደገበያው የተረጨ መሆኑ በራሱ የዋጋ ግሽበትን አምጥቷል። በኢኮኖሚው ውስጥ የሚዘዋወረው ገንዘብ የተረጨ ነው የሚል አተያይ አለኝ። ይህን ያስባሉኝ ምክንያቶች አሉ።ለምሳሌ ከሚንቀሳቀሰው ገንዘብ ሲታይና ካለው የፋይናንስ ተቋማት እንቅስቃሴም በመነሳት ነው። በተለይ ደግሞ ለምሳሌ የቁጠባና የብድር ወለድ ቢታይ በተለመደው የባንክ ስርዓት የቁጠባና የብድር ወለድ እኩል መሆን የለበትም፤ ነገር ግን እጅግ በጣም የተራራቁ ናቸው።

በአሁኑ ሰዓት ባንክ ነው ማስቀመጥ የምፈልገው የሚል ሰው እጅግ በጣም ትንሽ ነው የሚሆነው፤ ምክንያቱም ባንክ ሲያስቀምጥ እንደሚመስለኝ የሚያገኘው ሰባት በመቶ ነው። ይህ ደግሞ አሁን ካለው የዋጋ ግሽበት ብዙ ብር ባንክ እያስቀመጥን በሄድን ቁጥር ብዙ እያጣን እንሄዳለን ማለት ነው። ስለዚህ ሰው በእጁ ላይ ያለውን ገንዘብ የመጠቀም ሁኔታ ነው ያለው፤ በእጅ ላይ ገንዘብ ማኖር የሚያመጣው ደግሞ ወደ ገበያው ገንዘብ መርጨትን ነው። ወደ ኢኮኖሚው ብዙ የሚንቀሳቀስ ገንዘብ ከገባ ደግሞ በተዘዋዋሪ ለዋጋ ግሽበቱ የራሱን ሚና ይጫወታል ይላሉ።

በሌላ መልኩ ደግሞ የምግብና የነዳጅ አቅርቦት ዋጋ መጨመር በብዙ የእኛ ብር ትንሽ ዶላርን እንዲያባርሩ ማድረግና የእኛ ገንዘብ በየጊዜው የመግዛት አቅሙ እንዲወርድ ያደርጋል። ይህ የብር አቅም መውረድ እንደ እኛ አገር ባሉ አገሮች ላይ ሰው የዶላር ዋጋን ባንክ የሚለውንና በጥቁር ገበያ የሚባለውን እንዲያውቅ አድርጎታል። ሰው ይበልጥ የሚከተለው ደግሞ የጥቁር ገበያውን ሆኗል። ይህ ደግሞ ለምሳሌ ባንክ 50 ቤት ቢገባና ጥቁር ገበያ ላይ ደግሞ 80 ቢገባ ይህን ወዲያውኑ ነጋዴው ወስዶ ሸማቹ ማህበረሰብ ላይ ነው የሚጭነው። ይህም ለዋጋ ግሽበቱ እጅግ በጣም የራሱ የሆነ ድርሻ አለው።

ይህም ሊሆን የቻለው የእኛ በምግብ ላይ በተለይ በግብርና ላይ በተገባን ልክ አለመስራታችንና እርሻችንም በዝናብ ላይ ተንጠልጣይ መሆን ሲሆን፣ ይኸውም አንድ ጊዜ በድርቅ ሌላ ጊዜ ደግሞ በጎርፍ የመመታቱ ጉዳይ አቅርቦትና ፍላጎት ላይ አለመመጣጠን እንዲፈጠር ያደርገዋል። ከዚህም የተነሳ የዋጋ ግሽበቱን በየጊዜው እንድናይ አድርጎናል ሲሉ ያብራራሉ።

ዶክተር አደሬ፣ የመጀመሪያው መፍትሄ ነው ብለው ያብራሩት፤ ሞኒተሪ ፖሊሲ ላይ መንግሥት አሁን እያደረገ ያለውን በደንብ አጥብቆ መቀጠል መቻል አለበት ሲሉ ነው። መንግሥት አሁን ብዙ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች በባንክ እንዲሆኑ አድርጓል። ቀደም ሲል ኢ-መደበኛ በሆነ ሁኔታ ሲንቀሳቀስ ገንዘብ ኢኮኖሚው ውስጥ ሲረጭ ነበር። አሁን አሁን ግን መንግሥት ሰዎች በባንክ እንዲጠቀሙ እያበረታታ ነው። ነገር ግን ብዙ ሰዎች ቅሬታ ያሰማሉ። ቅሬታው በፊት ከነበረውና ከምናውቀው ነባራዊ ሁኔታ ስለሚለይ እና ምናልባትም አዲሱ ሊመቸን አይችልም ብለው ከማሰብ የመጣ ነው።

ይሁን እንጂ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች በባንክ እንዲሆኑ መደረጉና ያንን መተግበሩ የዋጋ ግሽበትን ለመቆጣጠር የሚረዳ ነው። ይህ ደግሞ በብዙ አገሮች ላይ እየተተገበረ ያለ እንቅስቃሴ ነው። ይህ በእርግጥ በአጭር ጊዜ ውስጥ የዋጋ ግሽበቱን ይቆጣጠራል ማለት ሳይሆን በረጅም ጊዜ ትግበራ የሚያስተካክል ይሆናል የሚል እምነት አለኝ ሲሉ ይጠቁማሉ።

ሁለተኛውን መፍትሄ ሲናገሩ ደግሞ መንግሥት ወጪውን መቀነስ መቻል አለበት ይላሉ።መንግሥት በዚህ ላይ ጥሩ የሚባል እምርታ አሳይቷል። ጥሩ ተሞክሮዎችና ጥሩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው። ለምሳሌ መንግሥት ቢሮዎችን ወደ አንድ የማምጣት፤ በውጭ አገር ያሉ አንዳንድ ቆንስላ ጽህፈት ቤቶችን እንደየአስፈላጊነታቸው በከፊል የመቀነስ ነገር ሲያደርግ ወጪዎችን እንደመቀነስ ነው፤ ወጪ ሲቀነስ የትኩረት አቅጣጫው የዋጋ ግሽበቱን ወደማረጋጋት ማስኬድ ነው። ስለሆነም መንግሥት እነዚህን ጉዳዮች በተጠናና በተጠናከረ ሁኔታ ማስቀጠል አለበት፤ አንድ ጊዜ ጀምሮ የሚያቆመው መሆን የለበትም።

ሶስተኛው ደግሞ የቁጠባ ኢንተርስት ሬት ሲሆን፣ የቁጠባ ኢንተርስት ሬት በአንድ ጊዜ ሳይሆን ቀስ በቀስ መጨመር መቻል አለበት የሚል አስተያየት አላቸው። ሰዎች በመቆጠባቸው የሚያጡ ከሆነ ገንዘባቸውን ወደባንክ አምጥተው ከመቆጠብ ይልቅ ወደማጥፋት ነው የሚሄዱት። ስለዚህ ቀስ በቀስ በጥንቃቄ ተግባራዊ መደረግ መቻል አለበት።

በእርግጥ በአንድ ጊዜ ኢንተርስት ሬት የሚጨመር ከሆነ ግን ሰው ያለውን ገንዘብ በሙሉ ባንክ ያስቀምጥና በወለድ መኖር ይጀምራል። ምክንያቱም ገንዘብ ባንክ ሲቀመጥ ለባንክ እዳ ነው፤ በመሆኑም ባንኮቹን ደግሞ ሌላ እዳ ውስጥ እንዳንጥል በጥንቃቄ ቀስ ቀስ በማድረግ ምላሽ መስጠት በሚያስችል መልኩ ተግባራዊ ቢደረግ መልካም ነው።ከዚህ ጋር ተያይዞ የአከፋፈል ስርዓታችን መሻሻል መቻል አለበት፤ በተለይ ከካሽ ወደ መስመራዊ አከፋፈል ስርዓት መሄድ ተመራጭ ነው። አሊያም ገንዘብ በእጃችን ካለ ለማውጣት እንገፋፋለንና መንግሥት እዚህ ላይ የተጠናከረ ሥራ ቢሰራ ጥሩ ነው ብለዋል።

ደክተር አደሬ፣ አራተኛው መፍትሄ ብለው ያስቀመጡት ግብርናችን ላይ መስራት የሚለውን ነው። ምርትና ምርታማነትን እጅግ በጣም ማዘመን አለብን።120 ሚሊዮን ህዝብ የሚመግብና ለብዙዎቹም የሥራ እድል የፈጠረ በመሆኑ ዘርፉ ላይ መስራት በርካታ ነገሮችን የሚቀይር ነው በማለት ያስረዳሉ። መንግሥት የግል ዘርፉንና ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን በአንድ ላይ በማስተባበር ምግብ ማከማቸት ላይ መስራት አለበት። ምግብን ማከማቸት የሚቻለውን ማንኛውንም ምግብ ነክ ነገር ማከማቸት ያስፈልጋል። ከተከማቸ ክፍተት ወደታየበት አካባቢ በቀላሉ ማንቀሳቀስ ስለሚቻል የዋጋ ግሽበቱን መቀነስ ይችላል።

በመጨረሻ ግን ይህ ሁሉ ተደርጎ ነገሮች መስመር እስኪይዙ ድረስ በከተማው ይሁን በገጠር ላሉ በጣም ደሃ ለሆኑት የማህበረሰብ ክፍሎች ድጎማ መኖር መቻል አለበት። በተለይ ምግብና ለምግብ የሚውሉ ግብዓቶችን መንግሥት ቢደጉም መልካም ይሆናል ሲሉ ይመክራሉ።

በመፍትሄነት የተቀመጡትን ጉዳዮች ተግባራዊ ለማድረግ የምንቸገር አይመስለኝም የሚሉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው፣ ደግሞም ከእኛ አቅም በላይ አይሁንም የሚል እምነት ስላለኝ የከፋ ነገር አይገጥመንም ብዬ አምናለሁ ብለዋል። እንደ አገር መቀጠል ካለብን መረጋጋት ሰፍኖና ሁሉም ሰው በሰላም መኖር እንዲችል የምንፈልግ ከሆነ ከላይ በተጠቀሱት መፍትሄዎች ላይ የማንሰራበት ምክንያት የለንም ብለዋል።ከእኛ አቅም በላይ የሆኑ ነገሮች አሉ፤ ለምሳሌ የነዳጅ ዋጋ አንዱ ነውና ይህን ለመቋቋም ግን ለምሳሌ ግብርናችን ላይ በደንብ ብንሰራ መለወጥ እንችላለን። በተጨማሪም ሞኒታሪ ፖሊሲያችንም ላይ የምንሰራ ከሆነ የዋጋ ግሽበቱ የማይቀንስበት ሁኔታ የለም ሲሉ አስረድተዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# በጎ ፈቃድ አገልግሎት ያጎላት ኢትዮጵያ

**ሰላማዊት ውቤ**



ፎቶ፡ በፀሐይ ንጉሴ

**አራተኛው የዓለም በጎ ፈቃድ አገልግሎት ሪፖርት ይፋ ሲሆን**

በጎ ፈቃድ አገልግሎት በዓለም፣ በአህጉርና በአገር ደረጃ ባህል ተደርጎ መሠራት ከጀመረ በርከት ያሉ ዓመታት ተቆጥረዋል።በተለይም እንደ አህጉር አፍሪካ የተሻለ ሥራ እንደምታከናውን ይጠቀሳል።ከአፍሪካ ደግሞ ቀድሞ ባህሏ ያደረገችው ኢትዮጵያ ድንቅ ብቃቷን እንዳሳየች ሰሞኑን ይፋ የተደረገው ሪፖርት ያመላክታል።በተፈጥሮ ልበ ሩህሩህና አንጀተ እንስፍስፍ በሆኑ ሴቶች መጀመሩ ደግሞ እንድትጎላ ካደረጓት መካከል ይጠቀሳል።

ጅማሮው በአሜሪካን አገር እንደነበር ይወሳል።ምክንያቱ ደግሞ የእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት «የፈቃደኛ ቡድን» የተሰኘ ስያሜ ያላቸውና ቁጥራቸው የተበራከተ ሴቶች ለወታደሮችና ለጦር ጉዳተኞች ጊዚያቸውን ሰውተው ነፃ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስጠታቸው ነው።እኤአ በ1881 ባርተን የአሜሪካ ቀይ መስቀልን ሲመሰርት እኤአ በ1889 ደግሞ በጆንስተውን የውሃ መጥለቅለቅ ለተጎዱ ሰዎች እርዳታዎችን በማሰባሰብ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተጀምሯል። በዚህ ተሳትፎ ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ይልቅ ሴቶች አይነተኛ ሚና ተጫውተዋልና ነው።ለዚህም ነው በጎ ፈቃድ አገልግሎትን ሴቶች ጀምረውታል የሚባለው።

አሁን ላይ በዓለም ደረጃ በአገልግሎቱ ዙርያ ሴቶች እያደረጉት ያለው አስተዋጾ ብዙ ነው። እሩቅ ሳንሄድ በአገራችን ውስጥ ብቻ ብዙ ሩህሩህና ደጓሚ ሴቶችን በብዛት እንመለከታለን።በለውጡ ዓመታት ብቻም የሴቶችን ድጋፍ ብናይ ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል የተለየ እንደሆነ መናገር ይቻላል።ምክንያቱም ሴቶች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉት ያለምክንያት አይደለም።በብዛት ተጎጅም ተጠቃሚም ስለሚሆኑ ነው።

በአራዳ ክፍለ ከተማም ሆነ ሠሜን ማዘጋጃ አካባቢ የዶሮ ተራ መንደርተኛ የሆኑት ወይዘሮ ተዋበች አንዳርጌ ለዚህ ትልቅ ማሳያ ናቸው።ምክንያቱም እርሳቸው የዚህ አካባቢ በጎ ፈቃድ አገልግሎት አንቂ ናቸው።ሥራ በማስተባበር አይነተኛ ምሳሌም እንደሆኑ ይነገርላቸዋል።ከዚህ ጋርም ተያይዞ እንዳሉን፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ባህሉ ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን አዲስ አይደለም።ሁልጊዜ በአገር ጉዳይ ማንም ወደኋላ አይልም።ለዚህም ማሳያው የአካባቢያችን ሴቶች በጥፋት ኃይሉ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች አለሁላችሁ ማለታቸው ነው።ለመከላከያም ቢሆን ከልጆቻቸው ጉሮሮ ቀንሰው የሰጡ መሆናቸው በጎ ፈቃደኝነታቸውን ያሳየናል።

«በድንበር ተሻጋሪ በጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደ ሶርያ የፈረሱ አገር ዜጎች ጭምር መደገፍ አለባቸው ብዬ አምናለሁ» የሚሉት ወይዘሮ ተዋበች፤ ከአዲስ አበባ ከተማ አልፈው በሰሜን ሸዋ ዞን ደብረ ብርሃን ከተማ ተጠልለው ለሚገኙና ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ ወገኖች 14 ኩንታል ምግብና የተለያዩ ቁሳቁሶች በግላቸው አሰባስበው የሰጡ ናቸው። በዚህ ደግሞ እሳቸው የሚኖሩበት ህንፃ (ብሎክ) 81 እማወራዎች በተግባሩ ሲሳተፉ መቆየታቸውንም አውስተውናል።

«ሴቶች በችግር የበለጠ ተጎጂና ተጋላጭ ናቸው» ያሉን ወይዘሮ ዘሀራ ጀማል በበኩላቸው፤ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተሳታፊና ተጠቃሚነት ቀዳሚዎቹ ሴቶች መሆናቸውን ያስረዳሉ።ለዚህም በማስረጃነት የሚጠቅሱት በ1967 ዓ.ም የተደረገው የዕድገት በሕብረት ዘመቻን ነው።እርሳቸውም አንዷ እንደነበሩ ያነሳሉ።ምክንያቱም 12ኛ ክፍልን ማጠናቀቅ በጎ ፈቃድ አገልግሎቱን መስጠት ሲቻል ብቻ ነው።በዚህም ወጣቶች ሴቶችን ጨምሮ ወደ ሁሉም የአገሪቱ ገጠራማ ክፍል ተልከው አገልግሎቱን ይሰጣሉ።

እናት አርበኛ የሺእመቤት ምህረቴ ሴቶችን ማበርታት የሚችለው በጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደሆነ ይናገራሉ።ምክንያቱም እርሳቸውን በሕይወት እንዲቆዩ ያደረጋቸው ይህ አገልግሎት እንደሆነ ያውቃሉ።እንደውም « ይሄን ያደርግልኛል የምለው ልጅም ሆነ ዘመድ የለኝም። ዕድሜዬ በመግፋቱ አቅሜም ደክሟል። ከበሽታው ጋር ተጋግዞ አሁን ላይ ከአልጋዬ መውረድ ተስኖኛል። ሆኖም የአካባቢው ሴቶች ይመግቡና ይንከባከቡኛል። በተለይ ወጣቶች ክረምት በመጣ ቁጥር ቤቴን ይጠግኑልኛል። ዐውድ ዓመትም ሲሆን የሚያስፈልገኝን ያደርጉልኛል።እናም ክረምት የበጎዎች መፍለቂያ ነው፡፡» ይላሉ።

የሁሉም እናቶች አስተያየት በበጎ ፈቃድ አገልግሎት የበለጠ ተሳታፊም ተጠቃሚም የሆኑት ሴቶች መሆናቸውን ያመላክታል። ሆኖም የመጀመርያው የዓለም በጎ ፈቃድ አገልግሎት በተባበሩት መንግስታት ሥር እ.ኤ.አ ታህሳስ 5 ቀን 2011 በዓለም ዙርያ የሚገኙ 80 አገራትን አቅፎ በአሜሪካ ኒዮርክ ሲቋቋም ዓላማ ያደረገው ጾታ ሳይለይ በአጠቃላይ የሰው ልጆችን መታደግ፣ ማገዝና መደገፍ እንደሆነ ባለፈው ሳምንት ይፋ የተደረገው በአራተኛው የዓለም የ2022 የበጎ ፈቃደኝነት ሪፖርት አስታውሷል።

«እኩልና ሁሉን አቀፍ ማህበራትን መገንባት» በሚል መሪ ሀሳብ በአፍሪካ ሕብረተሰብ መካከል እኩልነትና አካታችነትን ታሳቢ አድርጎ የቀረበው ሪፖርት እንደሚያመለክተው፤ አገልግሎቱ የሴቶች ተጠቃሚነትን በጉልህ የሚያረጋግጥ ነው።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትሯ ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በመርሐ ግብሩ ላይ እንደተናገሩት፤ ከጥንት ጀምሮ በደቡብ አፍሪካ ኡቡንቱ በኢትዮጵያ ደቦ፣ ጂጌ፣ ወንፈል እየተባለ በእርሻ ወቅት በአረማ፣ በአጨዳ፣ በምርት ስብሰባ በድንገተኛ ተፈጥሯዊ አደጋ ሲከናወን የኖረው በመተጋገዝ መንፈስ የተቃኘ ነፃ አገልግሎት ነው።ይህ ደግሞ የበለጠ ሴቶችን ያሳትፋል።ከ2020 እስከ 2021 በኢትዮጵያ 21 ሺህ በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች የተለያዩ የልማት ሥራዎችን አከናውነዋል።

ችግኝ ተከላ፣ ለአንደኛና ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የማጠናከርያ ትምህርት መስጠት፣ ትራፊክ አገልግሎት፣ ስንቅ ዝግጅት፣ በጦርነት ለተጎዱ ወገኖች አልባሳትና ቁሳቁስ ማሰባሰብ፣ የአረጋዊያንን እና የአቅመ ደካሞችን ቤት ማደስ ካከናወኗቸው መካከል ይጠቀሳሉ የሚሉት ሚኒስትሯ፤ ከእነዚህ ወጣቶች ውስጥ በርከት ያለውን ቁጥር የሚሸፍኑት ሴቶች መሆናቸውን ተናግረዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ እነዚህ ወጣቶች ለ38 ሚሊዮን ሕዝብ አገልግሎት ሰጥተዋል። እዚህም ጋር በጦርነት፣ በአውሎ ነፋስ፣ በሌሎች ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋ ክስተቶች የበለጠ ተጎጂና ተጋላጭ የሚሆኑት ሴቶች እንደመሆናቸው በአገልግሎቱ አብዛኛው ተጠቃሚም ነበሩ።አገልግሎቱ በገንዘብ ሲተመን ከሰባት ቢሊዮን ብር በላይ ይሆናልም። ይሄን ያህል ወጪ ማዳን እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ላሉና ብዙ የልማት ሥራዎችን ማከናወን ለሚጠበቅባቸው የአፍሪካ አገራት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

በጎ ፈቃድ አገልግሎት 50 በመቶ አንዳንዴም በላይ ሴቶች ባሉበት በአፍሪካ ሕብረተሰብ መካከል ጾታን ጨምሮ በሁሉም መስኮች እኩልነትንና አካታችነትን በማረጋገጡ ረገድ የጎላ ድርሻ ይኖረዋል። አፍሪካን በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከዓለም የተሻለ ደረጃ ለመድረስ በማስቻሉም በኩል የራሱን ጉልህ ሚና መጫወቱን ሪፖርቱ እንደሚያሳይ አንስተዋል።

ነፃ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት በአፍሪካ በተለይም በኢትዮጵያ እንደ ባሕል በመያዝ የተለመደ እንጂ አዲስ አለመሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትሯ፤ ይህ አገልግሎት በሕብረተሰቡ ውስጥ በነበረው የተዛባ አመለካከት ሳቢያ ለረጅም ዘመናት ከትምህርት ገበታ ርቀው የነበሩ ሴቶች የትምህርት ዕድል አግኝተው ከመሐይምነት የተላቀቁበት ነው ብለዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ማብራሪያ፤ በ1967 ዓ.ም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከመመረቃቸው በፊት ታላቅ ንቅናቄ በመፍጠር ባደረጉት ዘመቻ ሕዝቡን ከመሐይምነት ለማላቀቅ በነፃ ሲያስተምሩት ቆይተዋል። በዚህም በኢትዮጵያ እስከ 90 በመቶ በመድረስ ተንሰራፍቶ የነበረውን መሐይምነት በአንድ ጊዜ ወደ 37 በመቶ ማውረድ ተችሏል። ይህ ደግሞ የሴቶችን ተጠቃሚነት ያሰፋ ነበርም።

ዶክተር ኤርጎጌ እንደሚሉት፤ በለውጡ ዓመታት በጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ አነሳሽነት ችግኝ በመትከል፤ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን ለመከላከል እንዲሁም አቅመ ደካሞችንና ገቢያቸው ዝቅተኛ የሆነና ምንም ዓይነት ገቢ የሌላቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች በመንከባከብና በመደገፍ ረገድ አገልግሎቱ ከፊቱ በተሻለ ሁኔታ ላይ ደርሷል። ዘላቂና የተቀናጀ እየሆነም መጥቷል።በተለይ ከጥንት ጀምሮ ሴቶች በጦር ግንባር ከመሰለፍ በተጨማሪ አብዝተው በሚሳተፉበት የጦርነት ወቅት ስንቅ ዝግጅትና ደጀንነት ነፃ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደ አገር ጉልህ ሚና መጫወት ተችሏል።

ዕውቀት፣ ጉልበትና ሀብትን በማቀናጀት አስደናቂና አመርቂ ውጤቶች እያስመዘገበ ያለውን የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እንደ አገርም ሆነ እንደ አህጉር አቀናጅቶና ዘላቂ አድርጎ ለማስቀጠል እየተሰራ እንደሆነ ያነሱት ሚኒስትሯ፤ የኢትዮጵያ መንግስት እንደ አህጉር ሕብረተሰቡ እርስ በእርስ በልማትና እድገት ጎዳና የሚያስተሳስርበትን የወጣቶች በጎ ፈቃድ አገልግሎት ፖሊሲ በ2004 ዓ.ም ማዘጋጀቱን እንደማሳያነት ጠቁመዋል።ሥራው አሁን ላይ አገልግሎቱን ተቋማዊ በማድረጉ ረገድ ያለውን ክፍተት ይሞላልም ብለዋል። እንደ አህጉርም በማስተሳሰር ዕውቅና ወደ የሚያገኝበት ደረጃ እንደሚያሸጋግረው፤ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አሸናፊነቱንም እንደሚያጎላው ዕምነታቸውን ገልጸዋል።

በተባበሩት መንግሥታት የምስራቅና የደቡብ አፍሪካ አገራት ቀጠና የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተጠሪ ሉሲ ዱንጉ በበኩላቸው፤ በጎ ፈቃድ አገልግሎት መንግስትና ትኩረት ያልተሰጣቸውን የማህበረሰብ ክፍሎችን የሚያገናኝ ድልድይ ነው። ምክንያቱም የተገለሉ ማህበረሰቦች ጋር በቀላሉ መድረስ ያስችላል ሲሉ የጥናት ግኝታቸውን ለታዳሚው አካፍለዋል።

በጥናታቸው እንዳመላከቱትም፤ አገልግሎቱ በአፍሪካ ሕዝቦች መካከል ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን፤ አካታችነትንና እኩልነትን ማምጣትና ማረጋገጥ የሚያስችል ነው።በተጨማሪም ትኩረት ያላገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች በተለይም የሴቶችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ለመፍታት አይነተኛ ሚናን ይጫወታል።በዚህም በአገልግሎቱ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ልምድ አላት። የተሻለችም ሆናለች።

ኢትዮጵያ መሐይምነትን በብዙ እጅ ከነበረበት መቀነስ ከቻለው የእድገት በሕብረት ዘመቻ ጀምሮ በሰው ሰራሽና በተፈጥሯዊ ክስተት አደጋዎችና ችግሮች ወቅትም ለሌሎች የአፍሪካና የዓለም አገራት አርአያ የሚሆን ልምድ ማካበቷንና በአገልግሎቱ አፈፃፀምም የተሻለች መሆኗን በጥናት ማረጋገጣቸውን የሚያነሱት ሉሲ፤ የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ተግባሩ ከጥንት ጀምሮ በአህጉሩ እንደ ባህል ተይዞ መቀጠሉ እንደሆነም አስረድተዋል።

የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጠቀሜታን አስመልክተው የተለያየ የዘር ስብጥር፤ አስተዳደግና አመለካከት ካላቸው ዜጎች ጋር አብሮ መሥራትና ልምድ መለዋወጥ ማስቻሉን የጠቆሙት ሉሲ፤ በጎ ፈቃደኝነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰዎች በአካባቢያቸው የማሕበረሰቡን ሕይወት ለማሻሻል የሚያከናውኑት ተግባር ነው።ስለሆነም በጥናታቸው ተጠቃሚነትን ያረጋግጣልም ብለዋል።

እንደመንግስት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተከናወነ እንደሚገኝ የገለፁት ደግሞ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ባለሥልጣን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ፋሲካ ሞላ ናቸው። እርሳቸው እንዳሉት፤ በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ማህበራት የበጎ ፈቃድ ሥራዎች በዓለም አቀፍና በብሔራዊ ደረጃ እየተሰሩ ይገኛሉ። ለአብነት ሮተሪ ኢንተርናሽናልን አንስተዋል። ኪዋንቪስ ኢንተርናሽናል፤ ሊዮን ኪውስ ኢንተርናሽናል፣ ጅብሊንግ ኢንተርናሽናል ድርጅቶች በ20ኛው ክፍለ ዘመን በመጀመርያዎቹ ዓመታት ተመስርተው የበጎ ፈቃደኝነት አውታርን ማስፋፋት የቻሉ ናቸውም ብለዋል።

እንደ አፍሪካ በተለይ በ2018 አገልግሎቱን ወደ ማህበረሰቡ በማውረድ ችግሮቹን እርስ በእርስ በመረዳዳት መቅረፍ የሚችልበትን አቅም መገንባት ተችሏል ያሉት አቶ ፋሲካ፤ እንደ ኢትዮጵያም ድሆችና አቅመ ደካሞችን ከመደገፍ ጀምሮ ደሳሳ ጎጆዎችን መጠገን፣ ችግኞች መትከልና ሰፋፊ እንደ እርሻ ያሉና ሌሎች የልማት ሥራዎችን በበጎ ፈቃድ አገልግሎት መስራት እንደተቻለ አንስተዋል።

ኢትዮጵያም ከአገር አልፎ በአፍሪካ አፈፃፀሟ የተሻለ የሆነውም በዚህ ምክያት እንደሆነ አብራርተዋል።እኛም ተግባሩ አብሮ ከመሥራትና ልምድ ከመለዋወጥ ባሻገር ሕብረተሰቡ በሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ያለውን የተዛባ ግንዛቤ ቀርፎ ለለውጥ ያድርገው በማለት ጽሑፋችንን ቋጨን።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

በሳንምታዊው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን በ1950 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ የነበሩ ጋዜጦችን ተመልክተናል። ገሚሶቹ ርዕሰ ዜናዎች የተጻፉበት መንገድና ዜናዎቹ የተጻፉበት መንገድ ባይጣረስም፤ ርዕሰ ዜናዎቹ በተጻፈበት መንገድ ዜናዎቹ የተሟሉ ሆነው ያልቀረቡ ነበሩ። ዜናዎቹ ከተነበቡ በኋላም ከዛስ ምን ሆነ የሚያሰኝ ጥያቄ ያስከትላሉ። ከሦስት ዓመት እርግዝና በኋላ 2ኪሎ ከ150 ግራም በሕክምና ቀዶ ጥገና በወጣላቸው ሴትዮ ስንገረም ስለተወለደው ህፃን ግን የሚለን የለም። ቁመቱ ሁለት ሜትር ከሩብ የሆነው የሐረር ሰው በርዕሰ ዜናው ከሆስፒታል ወጣ ቢለንም ስለቁመቱ ችግር እንጂ ስለጤናው ችግርና ሕክምና የሚለን የለም። የቀ.ኃ.ሥላሴ ቤተመጻሕፍት ስጦታ ማግኘቱ፣ በወሎ 50 ሺህ የዛፍ ጉድጓድ እንደሚቆፈር የሚነግረንን ዜናም አካተናል።

ኃይለማርያም ወንድሙ

### የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ የመፃሕፍት ስጦታ አገኘ

ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ቅጥር ግቢ የሚገኘው የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ቤተመጻሕፍት ፫፻ ልዩ መጻሕፍት ከቸኮስላቫኪያ መንግሥት አግኝቷል።

መጻሕፍቶቹንም፤ በኢትዮጵያ የቸኮስላቫኪያ ኤምባሲ ካልቸራል አታሼ ሚስተር ሀርቻካ ዝንዲኮ ፤ግንቦት ፲፪ ቀን ፤ወደ ዩኒቨርሲቲ ቤተመጻሕፍት ሔደው፤ ለኮሌጁ ሳይንስ ዲን ፤ለፕሮፌሰር ጃቦትንስኪ አስረክበዋል። የካልቸራሉ አታሼ መጻሕፍቱን ባስረከቡበት ወቅት፤ እነዚህ መጻሕፍት ለዩኒቨርሲቲው ጠቃሚ ሆነው ከተገኙ፤ የቸኮስላቫኪያ መንግሥት ተጨማሪ መጻሕፍት ለማበርከት ዝግጁ መሆኑን አስገንዝበዋል። ፕሮፌሰር ጃስቲን ኪም በሰጡት መልስ፤ መጻሕፍቱ ለዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ከፍ ያለ ጥቅም የሚሰጡ መሆናቸውን ገልጸው፤ እኔ የሳይንስ ፋክልቲ ዲን እንደመሆኔ መጠን፤ ለወደፊት ከቸኮስላቫኪያ መንግሥት የሚሰጡት መጻህፍት ሳይንስ ነክ ቢሆኑ በጣም ደስ ይለኛል በማለት፤ ከዚያ የነበሩትን አሳቁዋቸው። (አዲስ ዘመን ግንቦት 13 ቀን 1957ዓም)

### በጎፍ ተራራ ሳይ ፶ ሺ የዛፍ ጉድጓድ ይቆፈራል
### (ከኢትዮጵያ ወሬ ምንጭ)

ደሴ፤ በወሎ ጠቅላይ ግዛት ጽህፈት ቤትና ጠቅላይ ግዛቱ የእርሻ ሚኒስቴር ተባባሪነት ፤ የጎፍ በተባለው ተራራ ላይ ዛፍ ለመትከል ስለታሰበ፤ የተራራውን አቀማመጥ የጠቅላይ ግዛቱ እንደራሴ ክቡር ፊታውራሪ ማሞ ስዩም ተመለከቱ። በዚሁ ጊዜ የጠቅላይ ግዛቱ የእርሻ ሥራ ዳይሬክተር አቶ ክንድዬ ኃይሉ የኮምቦልቻ ማዘጋጃ ቤት ሹም አቶ ሽፈራው ወልደ ልዑልና ሌሎችም ሰዎች ከተራራ ጫፍ ድረስ ወጥተው አካባቢውን ተመልከተዋል።

የጠቅላይ ግዛቱ የደን ክፍል ኃላፊ አቶ ኃይሉ ዳኜ፤እስከ አሁን ድረስ ፲፰ ሺህ ጉድጓድ እንደተቆፈረና በጠቅላላው እስከ ፶ ሺህ ጉድጓድ ለማስቆፈር የታሰበ መሆኑን ለክቡር እንደራሴ ገለጹ።

ከዚህም ሌላ የዚሁ አጋር ም/ወረዳ ገዥ ሻምበል አሰፋ ወዳጄ በቦታው ተገኝተው ስለነበር፤ አነሳስተው ጉድጓድ በማስቆፈር ይህን የተቀደሰ ተግባር በመፈጸማቸው ፤ ክቡር እንደራሴው አመስግነዋል። ( ግንቦት 28 ቀን 1957)

### ፫ ዓመት አርግዛ በኦፕራሲዮን ተገላገለች

እመት አሰገደች መኩሪያ የተባሉ የ27 ዓመት ሴት፤ ሦስት ዓመታት ሙሉ በእርግዝና ከቆዩ በኋላ ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻ ፶፯ ዓ.ም የጳውሎስ ሆስፒታል ሀኪሞች በኦፕራሲዮን የተረገዘውን ከሆዳቸው አውጥተውላቸዋል። እመት አሰገደች ነዋነሪነታቸው በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት፤ በሶሬ ወረዳ፤ በጥሪባ ገብርኤል አጠገብ ነው። እርሳቸውም የአንድ ወንድና የአንድ ሴት ልጅ ወላጆች ሲሆኑ ፤አቶ ተከስተ በቀለ የሚባሉ የትዳር ጓደኛ አሉዋቸው። ትናንትና ከእመት አሰገደች መኩሪያ ሆድ የወጣው ሁለት ኪሎ ከ150 ግራም እንደሚመዝን ከሆስፒታሉ የተገኘው ወሬ ያስረዳል።

ስለዚሁ ጉዳይ አፕራሲዮን ያደረጉት የቅዱስ ጳውሎስ ሐኪሞች ዶክተር አርብራያዶቪችና ዶክተር ጎሮቪስቢያ ሲያስረዱ ያለቦታው ለተረገዘ ልጅ ሳይሆን ቀርቷል። ይህ እንደ ህፃን ያለ ነገር ያረፈበት ቦታ ከመጥበቡ የተነሳ በሴትዮዋ ላይ ጉዳት ለማስከተል ይችል ነበር ብለዋል።

እመት አሰገደች በበኩላቸው ሲናሩ ለሕክምና ናዝሬት ሆስፒታል ሄጄ ሐኪሙ ደምሽ አልቆ ነው ብሎኝ ተመልሻለሁ። እርግዝና መሆኑን ግን በደንብ አውቀው ነበር። ቢብስብኝ ጊዜ ይህ ሆስፒታል ይፈውሳል ፤ በነፃም ያክማል ማለትን በወሬ ስለሰማሁ፤ እዚሁ ልሙት ብዬ መጣሁ። አሁን ግን ከዚህ ስቃይ ሳልፈወስ አልቀርም በማለት ገልጸዋል።( ግንቦት 28 ቀን 1957)

### ለመጀመሪያ ጊዜ በአገራችን ቁንዶ በርበሬ ተተከለ

በኢትዮጵያ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ የቁንዶ በርበሬ ተክል መተከል መጀመሩን ጅማ የሚገኘው የእርሻ ሚኒስቴር መ/ቤት ገልጿል። የቁንዶ በርበሬው ተክል የተከሉት አቶ አካለወርቅ ልብነወልድ የእርሻ ሚኒስቴርና አቶ መንገሻ መኮንን የጅማ ጠቅላይ ግዛት ረዳት እንደራሴ ናቸው።

የቁንዶ በርበሬው ተከላ በጅማ ከተማ በስተምሥራቅ ሲል ከከተማው ስምንት ኪሎ ሜትር ካለው መልኮ ከተባለው ሥፍራ ላይ ሰኔ ፲ ቀን ተከናውኗል።

በዕለቱ በተደረገው የዛፍ ተከላ በዓል ፫ሺህ ፮፻ የቁንዶ በርበሬ ችግኞች ተተክለዋል። የቁንዶ በርበሬዎቹ ዛፎች የተተከሉበት ሥፍራ ፰ ሺህ ካሬ ሜትር ይሆናል። በዕለቱም ለዛ ተከላው በዓል የተገኘው ሕዝብ ብዛት አንድ ሺህ ያህል እንደሚደርስ ተገምቷል።

የጂማውን የእርሻ ሚኒስቴር መ/ቤት ጠይቀን እንደተረዳነው፤ ከሦስት እስከ አራት ሚሊዮን የሚሆኑ የዛፍ ችግኞች ተሰናድተው ለሕዝብ ሊታደሉ፤ በመጠበቅ ላይ መሆናቸው ተነግሮናል። የዛፍ ችግኞቹም ያገርና የውጭ አገር ሲሆኑ የዓይነት ብዛታቸውም አሥራ ሰባት መሆኑን ተረድተናል።

ይህን ዘንድሮ የተተከለው ቁንዶ በርበሬ ዛፍ፤ ፍሬ መስጠት የሚጀምረው ከአምስትና ስድስት ዓመታት በኋላ ነው። ማንም እንደሚያውቀው እስከዛሬ ወደ አገራችን ይገባ የነበረው ቁንዶ በርበሬ እየተቆላ በመሆኑ ለዘር የማይሆን ነበር። (ሰኔ 13 1957 ዓ.ም)

### ቁመቱ ፪ ሜትር ከ፳፰ ሳንቲም ሜትር የሆነው ሰው ከሆስፒታል ወጥቷል

ስለጀማል ሔሬድ ከዚህ በፊት በጋዜጣችን ገልጠናል፤ ጀማል ቁመቱ ሁለት ሜትር ከሩብ፤ ደረቱ አንድ ሜትር ከ፲፰ ሳንቲም ሜትር የሆነ ነው፤ ሦስት ሰዎች በቀን የሚበሉትን ጀማል ብቻውን ያቀላጥፈዋል ተብሏል።

ሲተኛ ደንበኛው የሰው አልጋ አይበቃውም፤ ከቅልጥሙ በታች ያለው እግሩ ከአልጋው ይተርፋል፤ ጀማል ደንበኛ የሰው ቁመት ካለው ሰው ጋር አብሮ ሲቆም ለሌሎች ረጅም የሚመስሉ ከጀማል ትከሻ በታች ይቀራሉ።(ግንቦት 25 ቀን 1957)

# ዓለም አቀፍ



## ሩሲያ ከአውሮፓ ህብረት ለዩክሬን የተለገሱ የጦር መሳሪያዎችን ማውደሟን አስታወቀች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ ከአውሮፓ ህብረት ለዩክሬን የተለገሱ የጦር መሳሪያዎችን ማውደሟን አስታወቀች።

ዩክሬን የሰሜን አትላንቲክ ቃል ኪዳን ጦር ወይም ኔቶን እቀላቀላለሁ ማለቷን ተከትሎ ከሩሲያ ጋር ይፋዊ ጦርነት ከጀመረች ከሶስት ወር በላይ ሆኖታል።

በዚህ ጦርነት ምክንያት ከ6 ሚሊየን በላይ ዩክሬናዊያን ዜጎች መኖሪያ ቤታቸውን ለቀው ሲሰደዱ 20 በመቶ የዩክሬን ክፍልም በሩሲያ ጦር ቁጥጥር ስር ወድቋል።

ጦርነቱን ተከትሎም አውሮፓ ህብረት፣ አሜሪካ እና ሌሎች አገራት በሩሲያ ላይ ከስድስት ሺህ በላይ ማዕቀቦች የተጣሉባት ሲሆን፤ ሩሲያም የአጸፋ እርምጃ በመውሰድ ላይ ትገኛለች።

ምዕራባዊያን አገራት ለዩክሬን የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን በመለገስ ላይ ሲሆኑ፤ ሩሲያም የተለገሱትን የጦር መሳሪያዎች በማውደም ላይ መሆኗን ገልጻለች።

ከሰሞኑ ከአውሮፓ አገራት ለዩክሬን የተለገሱ የጦር ተሽከርካሪዎችን እና ሌሎች የጦር መሳሪያዎችን ማውደሟን የአገሪቱ ዜና ወኪል ታስ ዘግቧል።

የሩሲያ ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን አሜሪካ እና ሌሎች ምዕራባዊያን አገራት ለዩክሬን የጦር መሳሪያ እንዳይለግሱ አሳስበው ልገሳቸውን ከቀጠሉ ግን እርምጃ መውሰድን እንደሚቀጥሉ አስጠንቅቀዋል።

በተለይም ምእራባዊያን አገራት ረጅም ርቀት ተወንጫፊ ሚሳኤሎችን እንዳይለግሱ የተናገሩት ፕሬዝዳንት ፑቲን ሩሲያ ደህንነቷን ለመጠበቅ ስትል እርምጃ ትወስዳለች ብለዋል።

አሜሪካ፣ ስፔን እና ሌሎች የአውሮፓ ህብረት አባል አገራት ለዩክሬን ሚሳኤሎች እና ሌሎች የጦር መሳሪያዎችን ለግሰዋል ተብሏል።

እንደ ሩሲያ መከላከያ ሚኒስቴር መግለጫ ከሆነ ምዕራባዊያን ለዩክሬን የጦር መሳሪያ በመለገስ ጦርነቱን የማራዘም እቅድ እንዳላቸው ተገልጿል።



## አሜሪካና ደቡብ ኮሪያ በጋራ በመሆን 8 የባላስቲክ ሚሳዔሉችን አስወነጨፉ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ በዛሬው እለት በጋራ ባደረጉት ወታደራዊ ልምምድ ላይ 8 የባላስቲክ ሚሳዔሎችን ማስወንጨፋቸው ተነግሯል።

አገራቱ በጋራ ያደረጉት የሚሳዔል ማስወንጨፍ ሙከራ ሰሜን ኮሪያ በትናትናው እለት ላካሄደችው የሚሳዔል ሙከራ ምላሽ መሆኑም ታውቋል።

አሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ ጥምር ጦር አዛዥ በሰጡት መግለጫ፤ በዛሬው እለት የተወነጨፉት ሚሳዔሎቹ “ታክቲካል ሚሳዔል ሲስተም” በመባል የሚታወቁ ሲሆን፤ በተለምዶ የጃፓን ባህር ተብሎ ወደሚጠራው የምስራቅ ባህር ነው የተወነጨፉት ብለዋል።

“ጠራችን ሰሜን ኮሪያ ዓለም አቀፍ ህጎችን በመጣስ የምታካሂዳቸው ተከታታይ የባላስቲክ ሚሳዔል ሙከራዎች ያወግዛል” ያሉት አዛዡ፤ ከዚህ ተግባሯ በአፋጣኝ እንድትቆጠብም አሳስበዋል።

ሰሜን ኮሪያ በትናትናው እለት ብቻ ስምንት የባላስቲክ ሚሳዔሎችን ወደ ምስራቅ የባህር ክልሏ ማስንጨፏ ይታወሳል።

ሚሳዔሎቹ ከምድር ከ25 እስከ 90 ኪሎ ሜትር ከፍታ ላይ ከ110 እስከ 600 ኪሎ ሜትር ያክል ርቀት መብረራቸውም ተገልጿል።

ሰሜን ኮሪያ የባላስቲክ ሚሳዔል ሙከራውን ያደረገችው አሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ በፊሊፒንስ ባህር ላይ ስያካሂዱ የነበሩትን የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ማጠናቀቃቸውን ተከትሎ እንደሆነ ተነግሯል።

የአሜሪካ እና የደቡብ ኮሪያ ባለስልጣናት በጋራ በሰጡት መግለጫ፤ ሰሜን ኮሪያ በአገሪቱ ሰሜን ምስራቅ በምትገኘው ፑንጌይሪ ከተማ አቅራቢያ የኒውክሌር ሙከራ ለማድረግ እየተዘጋጀች እንደሆነ ምልክቶች ታይተዋል ብለዋል።

ሰሜን ኮሪያ በያዝነው ዓመት የተገመተውን የኒውክሌር ሙከራ ካካሄደች ከፈረንጆቹ 2006 ወዲህ ብቻ ለ7ኛ ጊዜ እንደሚሆንም ይጠበቃል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት:- www.press.et
ፌስቡክ:- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
# ስፖርት
ማክሰኞ

ይህ ቦታ ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ነገ ይጀመራል

- በውድድሩ የሚሳተፈው የኢትዮጵያ ቡድን ተሸኝቷል

**ቦጋለ አበበ**

ለ22ኛ ጊዜ በሞሪሽየስ በሚካሄደው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ላይ ኢትዮጵያን የሚወክለው የአትሌቲክስ ልዑካን ቡድን እሁድ ምሽት በአራራት ሆቴል ተሸኝቷል። ልኡካን ቡድኑ ትናንት ወደ ሞሪሽየስ አቅንቶም በሰላም መድረሱን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አሳውቋል፡፡

በሽኝት መርኃ ግብሩ ላይ የቡድኑ የአንድ ወር የሆቴል ቆይታውን በተመለከተ አትሌቶች፣ አሰልጣኞችና የቴክኒክ ቡድን መሪው አቶ አሰፋ በቀለ በየተራ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት ኮማንደር ደራርቱ ቱሉ እና የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ድኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት በመርሃግብሩ ላይ ተገኝተው ንግግር በማድረግም ለቡድኑ የሥራ መመሪያና የመልካም ምኞት መግለጫ መልእክት አስተላልፈዋል። የቡድኑ ተወካዮችም የአገር መለያና ምልክት የሆነውን ሰንደቅ አላማ ከታላቅ አደራ ጋር ከክብር እንግዶችና ከፌዴሬሽኑ አመራሮች እጅ ተረክበዋል።



የቡድኑ ተወካዮች የኢትዮጵያን ሰንደቅ አላማ ከታላቅ አደራ ጋር ከክብር እንግዶችና ከፌዴሬሽኑ አመራሮች እጅ ተረክበዋል፣

በ2020 በአልጄሪያ አዘጋጅነት ሊካሄድ የነበረው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለሁለት አመት ከተራዘመ በኋላ ዘንድሮ አዘጋጅ አገር ተቀይሮ በሞሪሺየስ ከነገ ጀምሮ ለተከታታይ አራት ቀናት ይካሄዳል። ኢትዮጵያ በዚህ ቻምፒዮና ጥሩ ውጤት አስመዝግባ ለመመለስ ከሃምሳ በላይ አትሌቶችን ከአንድ ወር በላይ ስታዘጋጅ መቆየቷን ከፌዴሬሽኑ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡ በዚህም ከሜዳ ተግባራት ውድድሮች ጀምሮ፣ በአጭርና መካከለኛ፣በሦስት ሺ ሜትር መሰናክል እንዲሁም በረጅምር ርቀት ውድድሮች በሁለቱም ፆታ ጠንካራ ተፎካካሪና ውጤታማ የሚሆኑ አትሌቶችን ወደ ውድድሩ ስፍራ መጓዛቸው ታውቋል፡፡

በአፍሪካ ትልቁ በሆነው የአትሌቲክስ መድረክ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከሃምሳ በላይ አገራት የሚሳተፉ ሲሆን በተለያዩ ውድድሮች በርካታ ሜዳሊያዎችን በመሰብሰብ ቀዳሚ ሆነው ለማጠናቀቅ ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተዋል።

በዚህ ቻምፒዮና በሃያ ሶስት የውድድር አይነቶች አርባ አምስት ፉክክሮች የሚስተናገዱ ሲሆን ሃያ ሁለት በወንዶች መካከል፣ ሃያ ሁለት በሴቶች መካከልና አንድ የአስር ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ውድድር በድብልቅ ጾታ ፉክክር የሚደረግ ይሆናል።

ከሜዳ ተግባራት ውድድሮች በተጨማሪ በሩጫ ውድድር ከአጭር እስከ ረጅም ርቀት የተለያዩ ፉክክሮችን የሚያስተናግደው ይህ ቻምፒዮና በአፍሪካ ታላላቅ አትሌቶች በብዛት ባይሳተፉበትም በርካታ ተስፋ የተጣለባቸው ወጣት አትሌቶች አገራቸውን በመጪው ክረምት በአሜሪካ ፖርት ላንድ ኦሪገን በሚካሄደው የአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለመወከል ራሳቸውን ያሳዩበታል ተብሎ ይጠበቃል። በተለይም በአለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና አገራቸውን ለመወከል በተለያዩ ርቀቶች ሚኒማ እስካሁን ማሟላት ያልቻሉ አትሌቶች በዚህ ውድድር የሚያስመዘግቡት ሰአት ወደ ታላቁ ውድድር ስለሚመራቸው ጠንካራ ፉክክር እንደሚያደርጉ ይጠበቃል። በተለያዩ የአጭር ርቀት እንዲሁም የሜዳ ተግባራት ውድድሮች በአለም ቻምፒዮና ለመሳተፍ ሚኒማ ማሟላት ዘወትር የሚከብዳቸው እንደ ኢትዮጵያውያ ያሉ አገራት በዚህ ቻምፒዮና በለስ ከቀናቸው በአዳዲስ የውድድር አይነቶች ሚኒማ አሟልተው በአለም ቻምፒዮና አዲስ የተሳትፎ ታሪክ ለመጻፍ እድላቸውን ይሞክራሉ።

የአፍሪካ አትሌቲክስ መዲና በመባል የምትሞካሸው ሞሪሽየስ ይህን የአፍሪካ ታላቅ የአትሌቲክስ መድረክ ለማስናዳት በቂ ዝግጅት ያደረገች ሲሆን እኤአ በ2019 የገነባችው ኮት ደ ኦር ብሔራዊ ሁለገብ ስቴድየም እንግዶቹን ይቀበላል። ሞሪሽየስ የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮናን እኤአ በ1992 እና በ2006 በስኬት ማስተናገዷ የዘንድሮው ቻምፒዮና ከአልጄሪያ ተነጥቆ የአዘጋጅነት እድሉ እንዲሰጣት ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

## ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በቁጠባ ብዙዎች ሃብት እንዲያፈሩ ያስቻለው ዩኒየን

**በአስምነህ ቸርነት**

ሦሰር ኃላፊነቱ የተወሰነ የገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ስራ ዩኒየን በአማራ ክልል በዳንግላ ከተማ መጋቢት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የተመሰረተ ነው ።በዳንግላ ወረዳ፣ በዳንግላ ከተማ፣ በፋግታ ለኮማ ወረዳ፣ በጃዊ ወረዳና በእንጅባራ ከተማ አስተዳደር የስራ ክልሉ አድርጎ በመስራት ላይ ያለው ሦሰር ዩኒየን 313 መሰረታዊ ማህበራትንና 85 ሺ 530 ወንድ እና 21 ሺ 777 ሴት በድምሩ 107 ሺ 407 አባላትን በማቀፍ አጠቃላይ ቋሚና ተንቀሳቃሽ ሃብቱ ወደ 594 ሚሊዮን 520 ሺ163 ብር እና የካፒታል መጠኑን 79 ሚሊዮን 45 ሺ 727 ብር አድርሷል ።ዩኒየኑ እስከ 2014 ዓ.ም 504 ሚሊዮን 869 ሺ190 ቁጠባ ያሰባሰበ ሲሆን 847 ሚሊዮን 361 ሺ535 ብር የብድር ስርጭት አከናውኗል ።ከዚህ የብድር ስርጭት ውስጥ አነስተኛና ጥቃቅን ንግድ ሥራዎች 69 በመቶ ሽፋን ሲኖረው ግብርና 17 በመቶ እንዲሁም የመኖሪያ ቤት ግንባታና የህንጻ ስራ 14 በመቶ ይሸፍናል፡፡

በብድር አቅርቦቱ በበርካታ መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራትና አባላት በተናጠል በእንስሳት እርባታና ማደለብ፣ በንብ እርባታ፣ በዶሮ እርባታ፣ በትራንስፖርት አገልግሎት፣ በወፍጮ አገልግሎት፣ በመኖሪያ ቤት ግንባታ፣ በሸርክና በገበያ ማዕከል ግንባታ፣ በአነስተኛ ንግድ ስራዎች፣ በሆቴል አገልግሎት፣ በደን ልማት፣ በወተት ተዋጽኦ ምርት፣ በማር ምርት፣ በብሎኬትና ቱቦ ምርትና በሌሎችም ዘርፎች ተሰማርተው የኑሮ ደረጃቸውን በእጅጉ ማሻሻል ችለዋል፤ ካፒታላቸውንም በእጅጉ አሳድገዋል፤ የቤት ባለቤትም ሆነዋል።

ለአብነት ብንወስድ በበረይታ ቀበሌ የሸሞዴ ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት በእንስሳት እርባታና ማድለብ በስምንት ሺ ብር መነሻ ካፒታል አሁን ላይ ከአምስት ሚሊዮን ብር በላይ ሃብት ፈጥረዋል ።የጫራ አንድነት ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት በትራንስፖርት ዘርፍ 50 ሺ ብር መነሻ ብድር ወስደው ከ900 ሺ ብር በላይ ሃብት አፍርተዋል ።በኳንቻ ኳኩርታ ቀበሌ ከጅማ ዩኒቨርሲቲ ተመርቆ በዶሮ እርባታ ላይ የተሰማራ አባል በ40 ሺ ብር መነሻ ብድር አሁን ላይ ከ400 ሺ ብር በላይ ሃብት ፈጥሯል ።የዳንግላ ገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባላት በአራት ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ብር ብድር ወስደው በሸርክና ግራውንድ ፕላስ ሶስት የገበያ ማዕከል በዳንግላ ከተማ እየገነቡ ሲሆን በነፍስ ወከፍ ከ ሶስት ሚሊዮን ብር በላይ ሃብት አፍርተዋል፡፡ከገጠር መሰረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር በቁጠባ ሥርዓት ብድር በማግኘት በአሁኑ ሠዓት ከገጠር ወደ ዳንግላ ከተማ በሆቴል ንግድ ሥራ በመሰማራት በ 40 ሺ ካፒታል እና 120 ሺ ብር መነሻ ብድር ወስደው በአሁኑ ወቅት ወደ አንድ ሚሊዮን 204 ሺ 462 ሃብታቸውን ከማሳደግ ባለፈ ለስምንት ሰራተኛ የስራ እድል ፈጥረዋል ።በዝጉዳ ቀበሌ የወተቴ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል አርሶ አደር 25 ሺ ብር ብድር ወስደው በአካባቢው ደን ልማት ሥራ ላይ በመሰማራት በ11 ቃዳ መሬት ላይ ደን በማልማት በአሁኑ ወቅት የደን ሃብታቸው ከ385 ሺ ብር በላይ ይገመታል ።ከገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር አንድ አባል በ20 ሺ ብር መነሻ ብድር የእህል ወፍጮ አገልግሎት በመክፈት አሁን ሃብታቸውን ወደ 950 ሺ ብር አሳድገዋል፡፡

የሦሰር ዩኒየን ለሴቶች ትኩረት በመስጠት በሴቶች ብቻ የተመሰረተ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር አባል በማድረግ እየደገፈ ይገኛል ።በ2008 ዓ.ም በዳንግላ የተመሰረተው የእናቶች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበር በአጭር ጊዜ ውስጥ 484 አባላትና ከ10 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያፈራ ነው ።አባላትን ከ 50 ብር ጀምሮ እስከ ሰባት ሺ ብር በማስቆጠብ የቁጠባ መጠኑን ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ አሳድጓል ።በግለሰብ ደረጃ ለ174 አባላት የብድር ስርጭት ያከናወነው ይህ የሴቶች ማህበር እስከ አሁን ድረስ 25 ሚሊዮን 784 ሺ 182 ብር የብድር ስርጭት አድርጓል ።አባላት ብድር ወስደው ለንግድ ስራ፣ ለግንባታና ለአነስተኛ ቁሳቁስ ተግባራት በማዋል ከዝቅተኛ ህይወት ወጥተው ኑሯቸውን



ዩኒየኑ በሚሰጣቸው ብድሮች የበርካታ አባሉቹን ሂወት መለወጥ ችሏል

ማሻሻል ችለዋል። ለአብነት ያህል ጉሊት መንገድ ዳር ሽንኩርት ይሸጡ የነበሩ ሴቶች አሁን ላይ ሱቅ ከፍተው ማከፋፈል የጀመሩ፣ ከኪራይ ቤት ተላቀው የቤት ባለቤት የሆኑ፣ መኪና መግዛት የቻሉ አባላት አፍርቷል፡፡

ዩኒየኑ ሶፍትዌርን በመጠቀም ከማንዋል ወደ ሲስተም በመቀየሩ ለደንበኞች በአራት ቅርንጫፎቹ በሚሰጠው አገልግሎት ገንዘባቸውን በቀላሉ ማውጣት አስችሏቸዋል፡፡ ሙያተኞች መሰረታዊ ማህበራት ተከፋፍለው በቁጠባ ቀናቸው በመገኘት እንዲቆጥቡ በማድረግና ብድር እንዲመለስ ክትትል በማድረግ ይደግፋሉ ።ዩኒየኑ ከሌሎች አቻ ዩኒየኖችና ከባንኮች ጋር የፋይናንስ ትስስር ያደርጋል ።በአሁኑ ጊዜ በዩኒየኑ ከ18 ሺ በላይ ደንበኞች የባንክ ነክ አገልግሎት እያገኙ ይገኛል፡፡

በ2012/13 በጀት ዓመት የአፈጻጸም ግምገማ መሰረት ዩኒየኑ 12 ሚሊዮን 036 ሺ ትርፍ አግኝቶ በተከናወነው የትርፍ ክፍፍል ከፍተኛ 310 ሺ 740 ብር ዝቅተኛ 64 ብር መሰረታዊ ማህበራት አግኝተዋል ።ዩኒየኑ በአሁኑ ጊዜ የራሱን ዋና መስሪያ ቤት በዳንግላ ወረዳ G+5 ህንጻ በመገንባት ላይ ይገኛል፡፡

ለዩኒየኑ ስኬት ዋናዎቹ ምክንያቶች ጠንካራ ተቋማዊ አደረጃጀት መፍጠሩ፣ ለአባላት ድጋፍ ልዩ ትኩረት ማድረጉ፣ አባላት ባንክ ነክ ሥራ እንዲሠሩ ማድረጉ፤ ጠንካራ አሰራር፤ አደረጃጀትና ተሣትፎ የሚያደርጉ አባላትን በመሸለም እርስ በእርስ ውድድር እንዲፈጠር ማድረጉና አባላት በራሳቸው አካባቢ የንቅናቄ መድረክ እንዲያዘጋጁ መደገፉ፤ በጊዜ ገደብ ቁጠባ የእምነት ተቋማት፣ የአርሶ አደር ማሰልጠኛ ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ ግለሰቦች እንዲቆጥቡ ማድረጉ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et